# 708/2013

# የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

12/2004

# የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ቁጥር 708/2013

ሰኔ 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ


መ ግ ቢ ያ .................................................. 1

ክፍል ፩

1. አጭር ርዕስ .................................................. 2
2. ትርጓሜ .................................................. 2
3. የመመሪያው ዓላማ.................................................. 4
4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን.................................................. 5

ክፍል ፪

5. መመሪያው የሚያራምዳቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች .................................................. 5
6. የመመሪያው ቁልፍ መርሆዎች .................................................. 6

ክፍል ፫

7. የመመሪያው አጠቃላይ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች .................................................. 9

ክፍል ፬

8. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር ሥልጣንና ተግባራት .................................................. 10
9. የመ/ቤቱ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት .................................................. 12
10. ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት .................................................. 13

ክፍል ፭

11. ግብረ-ኃይል ስለማቋቋም .................................................. 14
12. የግብረ-ኃይሉ አደረጃጀት .................................................. 14

ክፍል ፮

13. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ .................................................. 19
14. ለድጋፍና እንክብካቤ ብቁ ስለመሆን .................................................. 20
15. የድጋፍና እንክብካቤ ጥያቄ አቀራረብ .................................................. 21
16. የድጋፍ አሰጣጥ መስፈርቶች .................................................. 21
17. የድጋፍና እንክብካቤ ዓይነቶች .................................................. 21
18. በገንዘብ የሚደረግ ድጋፍ .................................................. 21
19. ድጋፍና እንክብካቤ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ .................................................. 22

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development and Construction

30/4/2009

ለሥርዓተ ፆታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ
ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡- የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፣

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥር በሚገኙ ሁሉም ቢሮዎች እና ጽ/ቤቶች ተፈጻሚ የሚሆነውን የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ቁጥር 16/2004 ሆኖ ከሰኔ 2004 ዓ.ም. ጀምሮ የፀደቀ መሆኑ ይታወቃል።

በዚሁ መሠረት የመመሪያውን አፈጻጸም እንድትከታተሉ የፀደቀው 1 ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጐ የተላከ መሆኑን እየገለጽን የሆነዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም እንድታስፈጽሙት እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የኮንስትራክሽን ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና የሚኒ-ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ
- ለከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮ
- ለመሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ ኤጀንሲ
- ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ፊጉላቶሪ ቢሮ
- ለከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ቢሮ
- ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
- ለመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመ የመንግሥት ሕንፃዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ
- ለድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ
- ለሕዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት
- ለተቀናጀ የመሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽ/ቤት
- ለኦዲት መምሪያ
- ለሕግ መምሪያ

ከ/ል/ኮ/ሚ/ር
ከአንድ ጥራዝ አባሪ ጋር

## ክፍል ፯


20. የዲሲፕሊን ጥፋት .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ... ... 23

21. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቶች .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ... ... 23


## ክፍል ፰


22. መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ..... 24

23. መመሪያውን ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .......... 24

24. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ........ 24

## መ ግ ቢ ያ

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት የዓለማችን ከፍተኛ ችግር ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ እያስከተለ ያለው ችግርም ከጤና ችግር በላይ በመሆን የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የፖለቲካዊ ቀውሶችን አስከትሏል፤ በማስከተል ላይም ይገኛል፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ከድህነት ለመውጣት፣ ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥና መልካም አስተዳደርን ለመገንባት የምታደርገውን ጥረት እየተፈታተነም ነው፡፡ ቫይረሱ እያስከተለ ያለው ሰብዓዊ ጉዳት አስከፊ ከመሆኑም በተጨማሪ መ/ቤቶች የሰለጠነ ባለሙያ እንዲያጡ፤ ሥራ ያልተሰራባቸው መደበኛ የሥራ ቀናት እንዲበዙ፤ ተተኪ የሰው ኃይል ለማሰልጠን የሚያስፈልግ ተጨማሪ ወጪ እንዲያድግ፤ የተቋማት የሕክምና፣ የካሣ ክፍያና የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ እንዲጎር፤ በአጠቃላይ የተቋማት የሥራ ውጤትና ትርፋማነት እያሽቆለቆለ እንዲሄድ ተፅዕኖ በማድረግ በሀገሪቱ አጠቃላይ ልማትና እድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

መንግስት የወረርሽኙን ስርጭት ለመግታትና እያስከተለ ያለውን ፈርጀ ብዙ ጉዳት ለመቀነስ በተቀናጀ ሁኔታ ለመቆጣጠርና ለመከላከል ይቻል ዘንድ ብሔራዊ ፖሊሲ በማውጣት እና ይህንንም ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ ህብረተሰቡንና የልማት አጋሮችን ያሳተፉ በርካታ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ እነዚህን ጥረቶች ይበልጥ አጠናክሮ ውጤታማ ለመሆን፣ በሥራ ቦታዎች የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ወጥነት ያላቸውና በሀገራዊው የጤና ፖሊሲ መርሆዎች ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ በተደረገው እንቅስቃሴ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ በሴክተሮችና በተቋማት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መመሪያዎች በመቅረጽ ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴርም ይህንኑ ሁኔታ አጠናክሮ በመቀጠል ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ሠራተኞች ተገቢውን ትኩረት ለመስጠትና የኤድስ ህመምተኛ ለሆኑት ደግሞ አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ ለማድረግ፣ በሀገራዊው የጤና ፖሊሲ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ አዘጋጅቷል ፡፡ ይህ መመሪያ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መ/ቤቶች የስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲችሉ በወጣዉ መመሪያ አራት ተራ ቁጥር 4.1 መሰረት ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል ፩

## ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የስራ ቦታ የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ቁጥር 708/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

ለቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፣

1) "ሚኒስቴር መ/ቤት" ማለት፡- በአዋጅ ቁጥር 691/2003 የተቋቋመው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነዉ።
2) "ሠራተኛ" ማለት፡- በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰዉ ነዉ።
3) "የበላይ አመራር" ማለት፡- የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር እና ሚኒስትር ዴኤታ ወይም እንደ አግባቡ ሌሎች የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችን ያመለክታል።
4) "የሥራ ቦታ" ማለት፡- የመ/ቤቱ ሠራተኞች ሥራቸዉን የሚያከናዉኑበት መደበኛ ስፍራ ነዉ።
5) "ኤች.አይ.ቪ" ማለት፡- ሰዉነት በተፈጥሮ በሽታን ለመቋቋምና ለመከላከል ያለዉን ችሎታ ወይም ብቃት የሚሸረሽርና ደረጃ በደረጃም ለበሽታዉ ወይም ለኢንፌክሽን የሚዳርግ ተህዋስ ነዉ።
6) "ኤድስ" ማለት፡- በኤች.አይ.ቪ. ሳቢያ ሰዉነት በተፈጥሮ ያለዉን በሽታን የመከላከል አቅም በማዳከም በማንኛዉም ተደራራቢ ኢንፌክሽን ከተያዘ በኋላ የሚከሰት የበሽታ መገለጫ ነዉ።
7) "ኤች.አይ.ቪ. በደሙ ውስጥ ያለበት ሰው" ማለት፡- አግባብ ካለዉ ባለስልጣን መ/ቤት ፈቃድ ባገኘ የምርመራ ተቋም የግለሰቡ የደም ናሙና ተወስዶ ደረጃዉን በጠበቀ የምርመራ ሂደት ቫይረሱ በደሙ ዉስጥ ስለመኖሩ የተረጋገጠ ግለሰብ ነዉ።
8) "የኤድስ ህመምተኛ" ማለት፡- በኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ሳቢያ ሰውነቱ በተፈጥሮ ያለው በሽታን የመከላከል ችሎታ መዳከም የተነሳ በሚከሰቱ የተለያዩ በሽታዎች የተያዘ ህመምተኛ ሰው ነው።

9) **"ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናት"** ማለት፡- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኛ ከነበሩ ሰው/ሰዎች ተወልደው በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ አንድ ወይም ሁለቱንም ወላጆቻቸውን ያጡ ዕድሜአቸዉ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት ናቸው፡፡

10) **"የኤች.አይ.ቪ. የደም ምርመራ"** ማለት፡- በደም ውስጥ ኤች.አይ.ቪ. መኖር ወይም አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚደረግ ደረጃውን የጠበቀ የደም ምርመራ ሂደት ነው፡፡

11) **"ቅድመ ምርመራ የምክር አገልግሎት"** ማለት፡- ለኤች.አይ.ቪ. የደም ምርመራ በፈቃደኝነት የቀረበ ሠራተኛ ምርመራ ከማድረጉ በፊት ለምርመራው የተነሳሳበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ የምርመራዉ ዉጤት በቀጣይ ሕይወቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያስከትል ተመርማሪው ሥነ-ልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርግ የሚረዳ የባለሙያ ምክር ነው፡፡

12) **"ድህረ ምርመራ የምክር አገልግሎት"** ማለት፡- በፈቃደኝነት የኤች.አይ.ቪ. ደም ምርመራ ላደረገ ሠራተኛ የደም ምርመራ ዉጤቱን መሠረት በማድረግ በባለሙያ የሚሰጥ የምክርና የሥነ-ልቦና ድጋፍ ነዉ፡፡

13) **"የአባለዘር በሽታ"** ማለት፡- በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ወቅት ከአንዱ ሰዉ ወደ ሌላዉ ሰዉ በረቂቅ ህዋስ ወይም ጀርም አማካኝነት የሚተላለፍ ኢንፌክሽን/በሽታ ሲሆን፤ ጨብጥን፣ ከርክርን፣ ባምቡሌን፣ ቂጥኝን፣ ያካትታል፡፡

14) **"ኮንዶም"** ማለት፡- በወንድ ብልት ላይ ወይም በሴት ብልት ዉስጥ የሚጠለቅ ቅባትነት ያለዉ ፕላስቲክ ሲሆን፤ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ወቅት ኤች.አይ.ቪ. ቫይረስን ጨምሮ ሌሎች የአባላዘር ተዋህስያንና ያልተፈለገ እርግዝናን የመከላከል ዕድል እንዲሰፋ የሚረዳ ነዉ፡፡

15) **"ግብረ-ኃይል"** ማለት፡- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስተባብርና የሚሰራ የአባላት ስብስብ/ግብረ-ኃይል ነው፡፡

16) **"ድጋፍና እንክብካቤ"** ማለት፡- ቫይረሱ በደማቸዉ ውስጥ የሚገኝ እና ህሙማን ሠራተኞች እንዲሁም ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናት የተሻለ አኗኗር እንዲኖራቸዉ እና ወረርሽኙንም በመቀነስ ረገድ የበኩላቸዉን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ የሚያግዝ ሰብአዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባር ነዉ፡፡

17) **"ምስጢር"** ማለት፡- የአንድ ሰዉ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ዉጤት ወይም የህመም ሁኔታ ከኤድስ ጋር ያለዉን ዝምድና የተመለከተ የሕክምና ሪኮርድ ወይም መረጃ በሚስጥር የሚያዝበትና ይፋ የማይወጣበት የአሰራር ሥርዓት ነዉ፡፡

18) **"የመከላከል ተግባር"** ማለት፡- መንስኤዉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሆነ የአንድ የጤና ችግር ወይም በሽታ የሚያስከትል ተህዋስ እንዳይዛመት ተገቢ ጥንቃቄ የማድረግ ተግባር ሲሆን፤ በሽታዉን ለመከላከል የሚደረግን ማንኛዉም የማስተማርና ሌሎች ተግባሮችን ያካትታል፡፡

19) **"መቆጣጠር"** ማለት፡- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት እና ሊያስከትል የሚችለዉን ጉዳት ለመቀነስና ባለበት ለማቆም የሚወሰድ እርምጃ ማለት ነዉ፡፡

20) **"ምቹ የስራ ሁኔታ መፍጠር"** ማለት፡- አንድ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኛ ቫይረሱ በደሙ ውስጥ መኖሩ በምርመራ ሲረጋገጥ ወይም ለሠራተኞች ሲገለጽ  የተመደበበት የሥራ ክፍል ከአካላዊና ከአእምሮአዊ የጤና ሁኔታዎች ጋር የተመቻቸ እንዲሆን ጥረት የማድረግ ወይም ወደ አመቺ ሥራ ማዛወር ወይም ሌሎች ተገቢ አስተዳደራዊ ድጋፎችን ማድረግ ነዉ፡፡

21)**"መረጃ"** ማለት፡- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ በሁሉም ዘንድ በግልጽ ሊታወቅ የሚገባ አሃዛዊ ጥንቅር ወይም ድፍን ገጽጽራዊ ትንታኔ የያዘ ወቅታዊ ዘገባ ነው፡፡

22) **"ትምህርታዊ ፕሮግራም"** ማለት፡- በተደራጀ መልክ መልእክትን ለሚመለከተዉ አድማጭ ወይም ተመልካች በተጠና ዉጤታማ የማስተላለፊያ መንገድ መግለጽ ነዉ፡፡

23) **"ጥናትና ምርምር"** ማለት፡- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ላይ የተገኘ ዕዉቀት፣ ሳይንሳዊ መረጃ፣ ግኝትና የነጠረ ሃሳብን ወዘተ... ለሌሎች ዉጤታማ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ ወይም በዚህ መነሻነት ተጨማሪ ዕዉቀትና ዛሣብ ለማግኘት የሚካሄድ ጥናት ነዉ፡፡

## 3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

የመመሪያዉ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡-

1) በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፤
2) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በስራ ቦታዎች ያለዉን አሉታዊ ተፅዕኖ በሚመለከት ግንዛቤ በማሳደግ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለዉጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ተግባራትን ለማካሄድ፣
3) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሠራተኞች፣ በቤተሰቦቻቸዉ እንዲሁም በዘርፉ እና መ/ቤቱ እያደረሰ ያለዉን አሉታዊ ተፅዕኖ በመከላከል ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ጥረት ለማድረግ፣
4) በቫይረሱ ምክንያት ሕሙማን ለሆኑ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች እንዲሁም በበሽታዉ ሳቢያ በሞት ለተለዩ የመ/ቤቱ ባልደረቦች ቤተሰቦች እንደአስፈላጊነቱና አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፍና እገዛ ለማድረግ፣
5) ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ህሙማን የሆኑ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች መድልዎ የማይፈጸምባቸው፤ ሰብዓዊ መብታቸው የተከበረ፤ ተገቢው ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ፤
6) በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ለአካለመጠን ያልደረሱ ህጻናት ልጆችና በአጠቃላይ ተጠቂ የህብረተሰብ ክፍሎች አቅም በፈቀደ መጠን የምግብ፣ የአልባሳት፣ የትምህርትና የጤና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሥራ አካባቢዎችና በሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ፪

## የመመሪያው ስትራቴጂክ ጉዳዮች እና መርሆዎች

## 5. መመሪያው የሚያራምዳቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች

1) ዘርፈ ብዙነት

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ያልነካው የሕብረተሰብ ክፍልና ተፅዕኖ ያላሳደረበት የኢኮኖሚ ሴክተር የለም፡፡ ስለሆነም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከናወኑ ማናቸውም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራሞች ሠራተኛውን ጨምሮ ሁሉንም የልማት አጋሮች ያቀፉና ንቁ ተሳትፎን ያረጋገጡ ሊሆን ይገባል፡፡ የሥራ ቦታዎችም ወረርሽኙን የመከላከል ተግባርን እንደመደበኛ ተግባር በመውሰድ ምላሽ መስጠት ይገባቸዋል፡፡

2) ባለቤትነት

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመግታትም ሆነ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ የሚቻለው በሥራ ቦታዎች በባለቤትነትና በኃላፊነት የመንቀሳቀስ ስሜት ሲኖር ነው፡፡ ስለሆነም የወረርሽኙን የአውዳሚነት ባህሪ በወል በመረዳት፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያውን እንደአስፈላጊነቱ በማሻሻል፣ የአፈጻጸም መመሪያዎችን በማዘጋጀት፣ ፈጻሚ አካላትን በማደራጀት፣ ዕቅድ በመንደፍ፣ በጀት በመያዝ፣ የአፈጻጸም መርሐግብር በማመላከትና የክትትልና የግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

3) ፈጣንና የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ማድረግ

ወረርሽኙ እስካሁን በሀገር ላይ ያደረሰው ጉዳት እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡ ስለሆነም በሀገሪቱ በሁሉም መስኮች የሚካሄደው የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዘመቻ አስቸኳይና የሁሉም የጋራ ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር ሚኒስቴር መ/ቤቱም በፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ትግሉ ውስጥ ፈጣንና የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ፈጥሮ ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡

4) የስርዓተ ፆታ እኩልነት መብትን ማራመድ

ማንኛውም በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ላይ የሚደረግ እንቅስቃሴ ፆታ ተኮር ሊሆን ይገባል። በተጓዳኝም በሥራ ቦታ በሚካሄዱ የመከላከል፣ የድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት ሴቶችን እና ወጣቶችን በንቃት ማሳተፍ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል።

5) ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ከሚገኝ ወገኖች ጋር ይበልጥ መተባበር

ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ወገኖች ከግልና ከማኅበራዊ ልምዳቸው በመነሳት፣ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለማስተማር ከፍተኛ አቅምና ብቃት አላቸው። የምክር አገልግሎት፣ ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ለመስጠትም መሰልጠን ይችላሉ። ከዚህ አኳያ በሥራ ቦታዎች የሚካሄዱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከል እንቅስቃሴዎች በእነዚህ ወገኖች የነቃ ተሳትፎ ሊታገዝ ይገባል። ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ወገኖችን በፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ማሣተፍ የቫይረሱን ስርጭት ለመቀነስና የእነሱንም ሕይወት ለማሻሻል አስተዋፅዖ እንዳለው መገንዘብ ይገባል።

6) ውጤታማነት

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት ልማትን እና የእድገት ውጤቶችን የመሸርሸር ጫና ከማሳደሩም በተጨማሪ ያለንን ውስን ጥሪት በልማት ላይ እንዳናውል ያደርጋል። ስለሆነም ወረርሽኙን ለመዋጋት የሚደረገው እንቅስቃሴ ውጤታማ ይሆን ዘንድ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የተላበሰ አሠራር የማስፈን ጥረት ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡

7) አግባብ ያለው የሀብት አጠቃቀም

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ድህነት ስር እንዲሰድና እንዲባባስ ያደርጋል። በአፀፋውም ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭነትን ያሳድጋል። ወረርሽኙን ለመግታት የሚደረገው እንቅስቃሴ ሀገራዊ ሀብትን በአግባቡና በወቅቱ የመጠቀም ጥረትን ይጠይቃል። ስለሆነም በስራ ቦታ የሚካሄዱ ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎች የራስ ሀብትን በመፍጠርና በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል መርህ ላይ ተመርስተው ሊካሄዱ ይገባል።

## 6. የመመሪያዉ ቁልፍ መርሆዎች

1) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሥራ ቦታ ጉዳይም መሆኑን መቀበል፤

የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሥራ ቦታዎችና አጠቃላይ አገራዊ የልማት ችግር መሆኑን በመቀበል፣ ወረርሽኙ በመስሪያ ቤቱ ተልዕኮ አፈጻጸምና በሠራተኞች ኑሮ ላይ የሚያስከትለውን ፊርጀ ብዙ ተጽዕና ለመቋቋም በባለቤትነት ስሜትና በቁርጠኝነት ይንቀሳቀሳሉ።

2) በሥራ ቦታ መድልዎና ልዩነት አለማድረግ፤

የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞችና ሥራ ፈላጊ አመልካቾች ምንም ዓይነት መድልዎና መገለል አይደረግባቸውም፡፡

3) በሥራ ቦታዎች ስሥርዓተ ፆታ እኩልነት እና ልዩ ትኩረት ለሚሹ ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት፤

ሀ/ መ/ቤቱ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን እና ሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚነድፈው ማንኛውም ፕሮግራም በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መርህ ላይ የተመሰረተ እና የሴቶችን ተሳታፊነት የሚያጎለብት ይሆናል፡፡

ለ/ በተፈጥሯዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮች ምክንያት ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ወጣት ሠራተኞች እና የሥራ ባህሪዎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡

4) ጤናማና ምቹ የሥራ አካባቢ የመፍጠር ጥረትን ማጠናከር፤

የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ፕሮግራሞችን በመንደፍና በመተግበር የመስሪያ ቤቱ የሥራ ቦታዎች ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭትና ሌሎች የጤና ጠንቆች ሥጋት የፀዱ ምቹና ጤናማ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

5) የውይይት፣ የምክክርና የድርድር ባሕል ማዳበር፤

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሠራተኞች እና በሌሎች አጋር ድርጅቶች መካከል በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ በቅን ልቦናና በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረተ ወቅታዊ ውይይትና ምክክር ሊደረግ ይገባል፡፡

6) የኤች.አይ.ቪ. በደም ውስጥ መኖር ለሥራ ቅጥርና የሥራ ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እንደ ብቃት መስፈርት እንዳይወሰድ ተገቢውን ጥረት ማድረግ፤

ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራን ሊያስገድዱ አይገባም፡፡ ነባር ሠራተኞችም ከሥራቸው ባህሪ አኳያ የሚያደርጓቸው የጤና ምርመራዎች አስገዳጅ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራን አለማካተታቸውን መረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

7) የሠራተኞች የግል የጤና መረጃ በሚስጥር መያዝ እና ሚስጥር መጠበቅ፤

ሥራ አመልካቾችም ሆነ ነባር ሠራተኞች ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የተያያዙ የግል የጤና መረጃዎችን ያለፈቃዳቸው እንዲገልጹ ማስገደድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ የሠራተኞች የግል የጤና መረጃ በሚስጥር የሚያዝና ያለተመርማሪው የጽሑፍ ፈቃድ

ወይም አግባብ ያለው አካል በሚያቀርበው ህጋዊ ጥያቄ ካልሆነ በቀር ለሌላ ሶስተኛ አካል የማይገለጽ መረጃ ነው። በተመሣሣይ ሁኔታም ሠራተኞች ስለ ባልደረቦቻቸው ይህንን የመሰለ የግል የጤና መረጃ እንዲያሳውቁ ማስገደድ ሰብዓዊ መብትን የጣሰ ድርጊት ሆኖ ይወሰዳል። በሚ/ር መ/ቤቱ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራ ውጤትን ጨምሮ የሠራተኞች የግል የጤና መረጃ በሚስጥር ሊጠበቅ ይገባል።

8) በኤች.አይ.ቪ ምክንያት የሥራ ውል እንዳይቋረጥ ማድረግ፤

በማንኛውም ሁኔታ የኤች.አይ.ቪ በደም ውስጥ መኖር የሥራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አይሆንም። እንደ ሌሎች በሽታዎች ሁሉ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በሽታዎች ሕምምተኛ የሆኑ ሠራተኞች የጤና አቋማቸው ሥራ እንዲሰሩ ብቁ የሚያደርጋቸው እስከሆነ ድረስ በተመደቡበትና ባሉት ሌሎች ተስማሚ የሥራ መደቦች ላይ ተዘዋውረው የመስራት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

9) ወረርሽኙን በጋራና በቅንጅት መከላከል፤

ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍልና የልማት አጋሮችን በቅንጅት ያሳተፈና ቁርጠኛ አመራር ያለው ሀገራዊ ፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ውጤታማ መሆኑን ተሞክሮዎች ያስረዳሉ። ስለሆነም የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት በብሔራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች የተጠቀሱ የመከላከያ እርምጃዎች በሥራ ቦታዎች ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል።

በሥራ ቦታዎች ወረርሽኙን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ በዕቅድ የተደገፈ ሆኖ ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ሊደረግበት ይገባል። ይህ ዓይነቱ በሥራ ቦታዎች ወረርሽኙን የመከላከል ዘርፈ ብዙ ሥራ ወቅታዊ መረጃ፣ ትምህርት እና የባህሪ ለውጥ ተግባራትን፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የምክርና የደም ምርመራን፣ የተዛማጅ ሕመሞችን ህክምናን፣ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል ሥራን፣ የፀረ-ቫይረስ መድኃኒት አገልግሎትን፣ የአባለዘር በሽታዎችን የማከም ሥራን፣ የፆታ እኩልነት ከልማት ሥራዎች ጋር አካትቶ ተፈፃሚ ማድረግን፣ የሥራ ላይ መብቶች ጥበቃን፣ ጥናትና ምርምር ማድረግን፣ የሥራ አካባቢ ንፅህና መጠበቅን፣ ጤናማና ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠርን፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያዎችን ማውጣትና አስፈጻሚ ግብረ ሀይል ማደራጀትን፣ የኤድስ ፈንድን ማቋቋም፣ በጀት መያዝን፣ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት መዘርጋትን፣ በጉዳዩ ዙሪያ ከሌሎች አጋሮች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነትና ትብብር በማድረግ አቅም መገንባትን ...ወዘተ. ሊያካትት ይገባል።

10) በሥራ ቦታዎች ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፤

ድጋፍ እና እንክብካቤ በሥራው ዓለም ለሚካሄድ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምላሽ ፊር ቀዳጅ ዕርምጃዎች ናቸው። ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ሰዎችን ጨምሮ ሁሉም ሠራተኞች ሕግ ወይም የአስተዳደር ደንብ በሚፈቅደው መሠረት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞችን የመጠቀም፣ ጥቅማ ጥቅሞችን የማግኘት፣ የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች ተጠቃሚ የመሆን እና ተገቢ የሆነ አስተዳደራዊ ድጋፍና እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል።

ቫይረሱ በደማቸው በመኖሩ ምክንያት ተደጋጋሚ ሕመም የሚያጋጥማቸው ሠራተኞች የተራዘመ የሕክምና ፈቃድ እንዲያገኙ ማድረግን፣ የጤና አቋማቸውን ባገናዘበ መልኩ ጥቅማቸው ሳይጓደል ወደ ቀላል ሥራ የመዛወር ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል። ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ በሥራ ቦታዎች ለሠራተኞች የሚሰጡ የሕክምና፣ የድጋፍና እንክብካቤ ፕሮግራሞች (የጤና ክትትል፣ እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ ድጋፎች) በዋነኛነት በሠራተኛው የጋራ ስምምነት በሚዋጣ ወርሀዊ የኤድስ ፈንድ ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ ይገባል። በሥራ ቦታ የሚሰጠውን ድጋፍና እንክብካቤ በተቋሙ ውስጥ የተቋቋሙ የተለያዩ ኮሚቴዎችና ቢሮዎች ሊደግፉት ይገባል። በመ/ቤቱ የሚካሄዱ የድጋፍና እንክብካቤ ሥራዎች ከሌሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በሚገኝ የፋይናንስ እገዛ ሊካሄዱ ይችላሉ። እነዚህ ተግባራት በተቻለ መጠን የሠራተኛውን ቤተሰብ፣ የአካባቢውን ሕብረተሰብና በተለይም ወላጅ አልባ ሕጻናትን ሊያካትቱ ይገባል።

<u>ክፍል ፫</u>

## 7. <u>የመመሪያው አጠቃላይ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች</u>

1) በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚካሄዱ ማናቸውም ፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞች ሁሉንም የሚኒስቴር መ/ቤቱን ሠራተኞችና ኃላፊዎች የሚያሳተፉ እና የፈጣን ተግባራዊ ምላሽ መርህን ከግንዛቤ እንዲያስገቡ ማድረግ፤
2) በሠራተኛው ስምምነት የኤድስ ፈንድ በማቋቋም፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለተጐዱ ሠራተኞች እና ወላጆቻቸዉን ላጡ ህፃናት የሠራተኛ ልጆች የሕክምና፣ የመድሃኒት፣ የተመጣጣኝ ምግብና ሌሎች ድጋፎች በዘላቂነት እንዲያገኙ ማድረግ፤
3) በመ/ቤቱ የሚካሄዱ ፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞችን ከጤና ፕሮግራም ጋር የተቀናጁ ማድረግ፣

4) ወረርሽኙን ከመከላከል አኳያ የሥራ ላይ መብቶች ጥበቃን ሊያጠናክር የሚችል ወቅታዊ የመመሪያ ማሻሻያ ማድረግ፣

5) በሴክተሩ የሚካሄዱ የፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞች የአካባቢውን ሕብረተሰብ ወረርሽኙን የመከላከል ጥረት የሚደግፍ እንዲሆን ማድረግ፣

6) የመ/ቤቱ አመራር አካላት ወረርሽኙን በመከላከል ረገድ ትኩረት እንዲሠጡና በቁርጠኝነት እንዲሳተፉ ማድረግ፣

7) ቀጣይነት ያለዉና የባህሪ ለዉጥ ሊያመጣ የሚችል የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራም ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ፣

8) በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት በማመቻቸት ሠራተኛዉ ራሱን በማወቅ ዘመናዊ የአኗኗር ባህል እንዲያዳብር ማድረግ፣

9) በሠራተኛው ስምምነት የሥራ ቦታ የኤድስ ፈንድ በማቋቋም የሕክምና፣ የመድሀኒት፣ የፋይናንስና ሌሎች ማኅበራዊ ድጋፎች በዘላቂነት እንዲኖር ማድረግ፣

10) የተጠናከረ ፀረ-ኤድስ የአጋርነት ግንኙነትና የቴክኒክ ትብብር ሥርዓት እንዲመሰረት በማድረግ ሁለንተናዊ የማስፈጸም አቅም ለመገንባት የሚያግዝ የእዉቀት፣ የሎጂስቲክስና የፋይናንስ ድጋፍ የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸትና በጀትን በቁጠባና በዉጤታማነት መጠቀም፣

11) ከስራ ባህሪያቸዉ አኳያ ይበልጥ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭ የሆኑና በሚያስከትለዉ ጉዳት ተጎጂ ለሆኑ ሠራተኞች ትኩረት በመስጠት በመከላከሉ እንቅስቃሴ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ፣

12) የፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞች አፈጻጸምን ለመመዘን የሚያስችል ወቅታዊ የግምገማ ስርዓት መዘርጋት፣

## ክፍል ፬

## ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሥራ ቦታዎች በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር፣ ሠራተኞችና ቫይረሱ በደማቸው የሚገኙ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

8. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር ሥልጣንና ተግባራት፣

1) መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከፍተኛ የሆነ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና፣ ፖለቲካዊ ቀውስ እንደሚያስከትል በመገንዘብ ቫይረሱን የመከላከሉን ስራ የመደበኛ ስራዉ አካል በማድረግ

በእቅድ ተይዞና በጀት ተመድቦለት በተቀናጀ መልኩ ተካትቶ (mainstreaming) ተግባራዊ እንዲደረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና አፈጻጸሞችን በየደረጃው መገምገም፤

2) ለፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መመሪያ ተግባራዊነት መከበር እና መሥሪዕ ፈጣንና ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድና መቆጣጠር፤

3) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሥራ ቦታዎች ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ለችግሩ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞች እና የሥራ ቦታዎች ትኩረት እንዲሰጥ ማበረታታት፤

4) ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ሠራተኞች ከሌሎች ሠራተኞች ጋር እኩል መብትና ግዴታ ስላላቸዉ፦

   ሀ) በምልመላና በስራ ቅጥር ሥርዓት፤

   ለ) በሥራ ምደባ፤ በእድገት፤ ዝዉዉር፤

   ሐ) በደመወዝ ጭማሪና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች አሰጣጥ፤

   መ) በሥልጠናና በትምህርት ዕድል፤

   ሠ) ለሕዝባዊ አገልግሎት በሃላፊነት በመመረጥ፤

   ረ) የጤና አገልግሎት በመጠቀም፤

   ሰ) በሕግ፤ በአስተዳደር ደንብና ለሠራተኞች በተሠጡ ሌሎች መብቶች ላይ ምንም አይነት መድሎና ልዩነት እንዳይደረግ ማድረግ፤

5) ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችና ፕሮግራሞች የስርዓተ ፆታ እኩልነት መብትን የሚያራምዱና የሴት ሠራተኞችን ተሳትፎና ብቃት የሚያሳድጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

6) የማንኛዉም ሠራተኛ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ዉጤት ሁል ጊዜ በሚስጥር እንዲጠበቅ ማድረግ፤

7) መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚያደርጋቸዉ እንቅስቃሴዎች ሁሉም የሥራ ክፍሎች እንዲሳተፉ ማድረግ፤

8) ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ የሚገኝ ወይም የኤድስ ሕመምተኛ ሠራተኞች እና ቤተሰቦቻቸዉ አቅም በፈቀደ መጠን ማንኛዉንም ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ፤

9) በመ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፤

10) ሠራተኛዉ ኤችአይቪ/ኤድስን በዘላቂነት በባለቤትነት ስሜት ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲችል በተደራጀ መልኩ እንዲንቀሳቀስ የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠርለት ማድረግ፤

11) በመ/ቤቱ የሚካሄዱ ፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞችንና ተግባራትን አፈጻጸም የሚያስተባብር፣ የሚከታተልና የሚቆጣጠር የሥራ ክፍል እና የፆታ ስብጥርን የጠበቀና በፈቃዳቸው ለመሳተፍ የሚፈልጉና ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለ ሠራተኞችን ያካተተ፣ ከልዩ ልዩ

የሥራ ክፍሎች የተዉጣጣ ግብረ-ኃይል እንዲቋቋም ማድረግ፤ የቅርብ ግንኙነትም በመፍጠር ማጠናከርና ማበረታታት፣

12)አግባብ ካላቸዉ የሥራ ቦታ አጋሮች፣ ከመንግስት አስፈጻሚና ከፍትህ አካላት፣ ቫይረሱ በደማቸዉ ውስጥ በሚገኝ ወገኖች ከተመሰረቱ ማህበራትና ከሲቪል ማህበራት ጋር ቅንጅታዊ የትብብር ግንኙነት በመመስረት የጋራ ምክክር ሥርዓት መፍጠር፤

13)ወረርሽኙን በመከላከል፣ የሕክምና የድጋፍና እንክብካቤ እንዲሁም የሰብዓዊ መብት ጥበቃን የተመለከቱ ትምህርታዊ ዝግጅቶች እንዲካሄዱ መደገፍ፤

14)በመ/ቤቱ የሚካሄዱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራሞች በተቻለ አቅም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሠራተኞች ቤተሰቦችን ያካተቱ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤

15)በመ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራት በፆታ እኩልነት ላይ የተመሰረቱና አካል ጉዳተኞችን ከግንዛቤ ዉስጥ ያስገቡ መሆኑን ማረጋገጥ፤

## 9. የመ/ቤቱ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

1) የኤች.አይ.ቪ. መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን በማወቅ ለቫይረሱ ከሚያጋልጣቸው ሁኔታዎች እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን መጠበቅ፣

2) የቫይረሱን መስፋፋት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በተነደፉ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና መመሪያዎች ላይ በሚደረገዉ ውይይት ላይ በቅንነት በመሳተፍና ከስምምነት ላይ በመድረስ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ግንባር ቀደም ተሳትፎ ማድረግ፤

3) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በመ/ቤቱና በሠራተኞች ላይ የሚያደርሰዉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጽዕኖ ለመዳሰስና ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን መስጠት፤

4) በመ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል ቫይረሱ በደማቸዉ ዉስጥ የሚገኝና ሕመምተኛ ለሆኑ ሠራተኞች እንዲሁም ወላጆቻቸዉን በኤድስ ሳቢያ ላጡ ልጆች ድጋፍና እንክብካቤ ለማድረግ አቅም በፈቀደ መጠን የሙያ፣ የፋይናንስና የማቴሪያል ድጋፍ ማድረግ፤

5) በመ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ ወቅታዊ መረጃዎች፣ የባህሪ ለዉጥን ሊያመጡ የሚችሉ ትምህርታዊ የሥልጠና ፕሮግራሞች፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የደም ምርመራ፣ የኮንዶም አቅርቦት፣ ድጋፍና እንክብካቤ እንዲሁም የሕክምና አገልግሎት እንዲኖር እና መሰረታዊ የስራ ላይ መብቶች እንዲተገበሩ አስተዋጽዖ ማድረግ፤

6) ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ዉስጥ የሚገኝና የኤድስ ሕሙማን የሆኑ ሰራተኞች እንዲሁም ሥራ ፈላጊዎችን ሰብአዊ መብት ማክበር፣ የአድልዎና የማግለል ተግባር አለመፈጸም፣ ተገቢዉን ፍቅር፣ ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፤

7) በመ/ቤቱ ምቹ የስራ ሁኔታን በመፍጠር የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመቀነስ የሚደረገዉን ጥረት መደገፍ

8) ከሥራ ባህሪያቸው አንፃር ከደምና ከሰውነት የውስጥ ፈሳሽ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሠራተኞች የተፈቀደላቸውን የአደጋ መከላከያ መሳሪያ በአግባቡ መጠቀም፤

9) በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች፣ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች፣ ምክክሮችና ወቅታዊ መረጃዎችን በንቃት መከታተልና ተግባራዊ ማድረግ፣

10) መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚያዘጋጃቸው የአሰራር ማዕቀፎች ላይ በንቃት መሳተፍ፣

11) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚካሄደውን ጥረት ለማሳካት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሞያ፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣

12) በሥራ ቦታዎች በሴት ሠራተኞች፣ ተለማማጅ ሰልጣኝ ሠራተኞች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሥራ ፈላጊ አመልካቾችና ተገልጋዮች ላይ ወሲባዊ ጥቃትና ትንኮሳ ከመፈጸም መታቀብ፣

13) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የሥራ ቦታ መመሪያውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፡፡

## 10. ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

1) መ/ቤቱ በሚያዘጋጃቸዉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር እንቅስቃሴዎች ዉስጥ በንቃት መሳተፍ፤

2) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ ልምድና ተሞክሮን በማጋራት በሥራ ቦታዎች የባህሪ ለዉጥ እንዲመጣ አርአያነት ያለዉ ተግባር ማከናወን፤

3) ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በየወቅቱ የምክር አገልግሎት ማግኘት እና የህክምና ክትትል ማድረግ፤

4) የበሽታዉን ስርጭት ከሚያባብሱ ድርጊቶች በመቆጠብና ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳይሠራጭ የበኩላቸዉን ጥረት ማድረግ፤

## ክፍል ፭

## በመ/ቤቱ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ግብረ-ኃይል አደረጃጀትና አሠራር

### 11. ግብረ-ኃይል ስለማቋቋም

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መ/ቤቶች የሥራ ቦታዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲችሉ ባወጣዉ መመሪያ ክፍል አራት፣ ተራ ቁጥር 4.1 መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭት መከላከያና መቆጣጠሪያ ግብረ-ኃይል ያቋቁማል።

### 12. የግብረ-ኃይሉ አደረጃጀት

1) የግብረ-ኃይሉ አባላት

የመ/ቤቱ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግብረ-ኃይል ተጠሪነቱ ለስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ሆኖ የሚከተሉትን አባላት ያካተተ ይሆናል።

ሀ/ የስርዓተ-ፆታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ኃላፊ - የግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ፤

ለ/ ከሁሉም የመ/ቤቱ የሥራ ክፍሎች የተወከሉ ሠራተኞች - አባላት፤

ሐ/ አንድ የተቀጠረ/የተመደበ ሠራተኛ (ፎካል ፐርሰን) አባልና ፀሐፊ ናቸዉ።

2) የግብረ-ኃይሉ ቢሮ

ግብረ-ኃይሉ ተግባርና ኃላፊነቱን በአግባቡና በተቀላጠፈ ሁኔታ መወጣት ያስችለዉ ዘንድ አንድ ቢሮ እና የእለት ተእለት ተግባራቱን የሚያከናውን መደበኛ ሠራተኛ ይኖረዋል።

3) የግብረ-ኃይሉ ተግባርና ሃላፊነት

ሀ/ግብረ-ኃይሉ የሚመራበትን የውስጥ ደንብ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የሥራ መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ በበላይ ኃላፊ ሲጸድቅም ተግባራዊ በማድረግ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ሐ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዳ የሥራ እቅድና አመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤ በእቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በማድረግ ለበላይ አመራሩ ሪፖርት ያቀርባል፣

መ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በዘርፉ ላይ የሚያሳድረውን ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ለመዳሰስና ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን በማሰባሰብ በመረጃ ላይ የተደገፉ ተግባራትን ለማከናወን የተለያዩ ጥናቶችን ያካሄዳል፣

ሠ/ የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት እንዲያስችል ተከታታይ ስልጠናዎች፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችና የውይይት መድረኮች ለሠራተኞች ያመቻቻል፣

ረ/ ሰራተኞች ራሳቸዉን ከኤች.አይ.ቪ. የሚከላከሉበትን እንዲሁም ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ሠራኞች እና ህሙማን ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ሰ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አኳያ ልምድ ለመቅሰም ከሌሎች አግባብ ካላቸዉ አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤ ለሥራዉ አስፈላጊ የሆኑ የሙያ፣ የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፍና የፕሮጀክት እገዛ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በበላይ አመራሩ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሸ/ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ህሙማን የሆኑ ሠራተኞች ሰብዓዊ መብት መከበሩንና ተገቢው ድጋፍና እንክብካቤ የተደረገላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

ቀ/ የብሔራዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሥራ ቦታዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የሚመለከቱ ሌሎች የፌዴራል የህግ ድንጋጌዎችና የሚኒስቴሩ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያና የውስጥ ደንብ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

በ/ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፈንድ ያቋቁማል፣

ተ/ ከመ/ቤቱ የበላይ አመራር የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ያከናውናል።

4) **የግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ ተግባርና ሀላፊነት**

የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግብረ-ኃይል ሰብሳቢ የግብረ-ኃይሉን ተግባርና ኃላፊነት በበላይነት ከመምራትና ከመቆጣጠር በተጨማሪ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ/ ቫይረሱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተነደፉ ፕሮግራሞችንና ዕቅዶችን በማጠናቀርና በማቀናጀት እንዲሠሩ ያደርጋል፤

ለ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሥራ ቦታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚካሄዱ ጥረቶችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሐ/ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሥልጠና መርሃ-ግብሮችን ይዘረጋል፣ የቅስቀሳና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ይሠራል፣ የማስተባበርና የማቀናጀት ተግባራትን ያከናውናል፤

መ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ የስራ ቦታ እቅዶችንና መርሃ-ግብሮችን አፈፃፀም በሚመለከት ተገቢዉን ክትትልና ግምገማ በማድረግ ለሚኒስቴሩ የበላይ አመራር ሪፖርት ያቀርባል፤

ሠ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጥር የወጡ እቅዶችን ማስፈፀሚያ የሚዉል ተጨማሪ የሃብት ምንጭ የሚገኝበትን መንገድ ያፈላልጋል፤

ረ/ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲበረታቱ ያደርጋል፤

ሰ/ በግብረሀይሉ የሚታወቁትን ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ የሚገኝና የኤድስ ህሙማን ሠራተኞች ማንኛዉም ጉዳይ በፈቃደኝነት ካልሆነ በስተቀር በሚስጥር እንዲያዝ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ሸ/ በተለየ ሁኔታ ለበሽታዉ ተጋላጭ የሆኑ አካላትን፣ ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ያገናዘበ ስልጠናና ትምህርት ይሰጣል/እንዲሰጥ ያደርጋል፤

5) የፎካል ፐርሰን ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/ ተጠሪነቱ ለግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ/ለስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ሆኖ የግብረ-ኃይሉን መርሃግብር መሰረት በማድረግና ከሰብሳቢዉ ጋር በመመካከር የዕለት ተዕለት ሥራዎች ያከናውናል፣ የግብረ-ኃይሉን የስብሰባ ጊዜ ያመቻቻል፣ ስለአፈፃፀሙም ለግብረ-ኃይሉ ወርሃዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፤

ለ/ ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አጋር መ/ቤቶችና ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ቫይረሱን በመከላከል ረገድ ትምህርታዊና ሠራተኛዉን አሳታፊ የሚያደርጉ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፤

ሐ/ የግብረ-ኃይሉን ቃለ ጉባኤና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፣ አደራጅቶ በመረጃነት ይይዛል፤

መ/ የግብረ-ኃይሉን ሥራዎች በመደበኛነት ያቀናጃል፣ ያመቻቻል፤

ሠ/ የግብረ-ኃይሉን ዓመታዊ እቅድና በጀት በማዘጋጀት በግብረ-ኃይሉ አፀድቆ ለበላይ አካል/ለስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ያቀርባል፤

6) የግብረ-ኃይሉ ሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

ሂሳብ ሹሙ ከግብረ-ኃይሉ አባላት መካከል የሚመረጥና ተጠሪነቱ ለግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ/ "በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፈንድ" በሚል ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤

ለ/ የሂሳብ ገቢና ወጪ በአግባቡ በመመዝገብ ይቆጣጠራል፤

ሐ/ በባንክ ሂሳብና ቼኮች ላይ ከግብረሀይሉ ሰብሳቢ ጋር በጣምራ ይፈርማል፤

መ/ ዓመታዊና የሶስት ወራት የሥራና የፋይናንስ ሪፖርት ለግብረሀይሉ አቅርቦ ያጸድቃል፤

ሠ/ አጠቃላይ የግብረሀይሉን የሂሳብ መዛግብት፣ ቼክን ጨምሮ ልዩ ልዩ ሰነዶችን በጥንቃቄ ይይዛል።

7) የግብረ-ኃይሉ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

ገንዘብ ያዥ ከግብረ-ኃይሉ አባላት መካከል የሚሰየም ሲሆን፣ ተጠሪነቱ ለግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች አሉት።

ሀ/ የግብረሀይሉን ገቢ ግብረ-ኃይሉ በሚያወጣቸዉ ህጋዊ ደረሰኞች ይሰበስባል፤

ለ/ ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰበዉን ገንዘብ በግብረሀይሉ የባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረግ ደረሰኞችን በጥንቃቄ ይይዛል፤

ሐ/ ለስራ ማስኬጃና ለግብረ-ኃይሉ ሥራ ጥቃቅን ወጪዎች የሚዉል ከብር 3000.00 (ሦስት ሺህ ብር) ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፤

መ/ የግብረ-ኃይሉን የየወሩን የወጪና ገቢ ሂሳብ ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን ያመሳክራል፤

ሠ/ በሂሳብ ሹሙና በግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ ጣምራ ፊርማ ሲታዘዝ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ/ እንዲከፈለዉ ለታዘዘለት ሰዉ ህጋዊ ደረሰኝ በመቀበል ወይም ለክፍያ በተዘጋጀ ሰነድ በማስፈረም ክፍያ ይፈጽማል፤

8) የሌሎች የግብረ-ኃይሉ አባላት ተግባርና ኃላፊነት

ከግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢና ጸሀፊ በተጨማሪ የሌሎች የግብረ-ኃይሉ አባላት ተግባርና ሃላፊነትን በተመለከተ እንደግብረሀይል አባልነታቸዉ አጠቃላይ የግብረሃይሉን መርህ፣ ዓላማና ዋና ዋና ተግባራት መሰረት በማድረግ በስብሰባዎች በመካፈል እና በዉይይት ዉሳኔዎችን በማሳለፍ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ሃላፊነታቸዉን መወጣት የሚጠበቅባቸዉ ሲሆን፣ በዋናነት ግብረ-ኃይሉ በሚመራበት የውስጥ ደንብ መሰረት እያንዳንዱ አባል የሚያከናውነዉ የሥራ ድርሻ ሊሰጠዉ ይችላል።

9) የግብረ-ኃይሉ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

ሀ/ ግብረ-ኃይሉ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ የሚኖረዉ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። በዓመት አንድ ጊዜ ከሠራተኞች ጋር አጠቃላይ ስብሰባ ይኖረዋል።

ለ/ የግብረ-ኃይሉ ስብሰባ በሰብሳቢዉ ወይም ሰብሳቢዉ በማይኖርበት ጊዜ እሱ በጽሁፍ በሚወክለዉ አባል ይመራል፡፡

ሐ/ ግብረ-ኃይሉ የሚያካሂደዉ የመደበኛ ስብሰባ ጥሪና አጀንዳ በግብረ-ኃይሉ ፀሀፊ አማካኝነት ቢያንስ ከስብሰባዉ እለት ሁለት ቀን በፊት ለተሰብሳቢዎች ሊሰጣቸዉ ይገባል፡፡

መ/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ለግብረ-ኃይሉ አስረድቶ ተቀባይነት ካላገኘ በስተቀር ማንኛዉም አባል የመደበኛም ሆነ የአስቸኳይ ስብሰባ ጥሪ ደርሶት መቅረት አይችልም፡፡

ሠ/ ያለ በቂ ምክንያት በተደጋጋሚ በስብሰባ የማይሳተፍ አባል ሲኖር ከአባልነት እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

ረ/ በማንኛዉም የግብረ-ኃይሉ ስብሰባዎች ከአባላቱ ከግማሽ በላይ (50+1) ከተገኙ ስብሰባዉ ይቀጥላል፡፡

ሰ/ ማናቸዉም የግብረ-ኃይሉ የስብሰባ አጀንዳዎች ዉይይት ተደርጎባቸዉ ዉሳኔ የሚያገኙት ከዕለቱ ተሰብሳቢዎች በሶስት አራተኛ ድምጽ የተደገፉ ሲሆን ብቻ ነዉ፡፡

ሸ/ ማንኛዉም የግብረ-ኃይሉ ስብሰባዎች በግልጽነትና በተጠያቂነት እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ዉይይት የሚካሄድባቸዉ ሲሆን፣ በፀሀፊው አማካኝነት ቃለ ጉባኤ ተይዞ ስብሰባዉ በተጠናቀቀ በሁለት ቀናት ዉስጥ ተሰብሳቢዎች ፊርመዉበት በሰነድነት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

10) **የግብረ-ኃይሉ የሥራ ክፍልና ልዩ ልዩ መገልገያዎች**

ሀ/ ግብረ-ኃይሉ መደበኛ ተግባሩን የሚያከናዉንበት ቢሮ ይኖረዋል፡፡

ለ/ የግብረ-ኃይሉ አባላት ሙሉ ጊዜአቸዉን ቢሮአቸዉ ዉስጥ ሆነዉ መደበኛ ሥራቸዉን ሲያከናዉኑ፣ ለተገልጋዮች ተገቢዉን አገልግሎት የሚሰጥ ፎካል ፐርሰን የተዘጋጀውን ቢሮ በመንግስት መደበኛ የሥራ ሰዓት ክፍት አድርጎ አገልግሎት ፈላጊዎችን ያስተናግዳል፡፡

ሐ/ ግብረ-ኃይሉ ለቢሮዉ ስራ ማከናወኛ ከመ/ቤቱ የሚሰጡትን ንብረቶች በሃላፊነት ተረክቦ በጥንቃቄ አገልግሎት ላይ ያዉላል፡፡

መ/ ለስራዉ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተጨማሪ የመገልገያ ቁሳቁሶችን፣ ግብረ-ኃይሉ ከበጎ አድራጊ ተቋማት በእርዳታ የሚያገኝበትን መንገድ በማፈላለግ እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

ሠ/ በእቅድ የያዛቸዉን ተግባራት ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑና ከሌሎች በድጋፍ /በስጦታ/ ማግኘት ያልቻለውን፣ የበጀት አቅሙ ለመግዛት የማያስችለውን የመገልገያ መሳሪያዎች ግዢ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀርባል፡፡

11) የውሎ አበል

የግብረ-ኃይሉ አባላት ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ስራ ጋር በተያያዘ ከአዲስ አበባ ከተማ ዉጪ ወደተለያዩ ስፍራዎች ሲንቀሳቀሱ የዉሎ አበል ይከፈላቸዋል፡፡

12) የግብረ-ኃይሉ የበጀት ምንጭ

የግብረ-ኃይሉ የበጀት ምንጭ፦

ሀ/ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመደብ መደበኛ በጀትና በስጦታ መልክ ከሚገኝ የማቴሪያልና ገንዘብ ድጋፍ፤

ለ/ ከሠራተኞች በፈቃደኝነት በየወሩ ከሚሰበሰብ መዋጮ፤

ሐ/ በበጎ አድራጊ ድርጅቶች ከሚደረግ የፋይናንስ፣ የማቴሪያል እና የገንዘብ እገዛ ...ወዘተ. ይሆናል፡፡

13) የግብረ-ኃይሉ የፋይናንስ አሰራር

ሀ/ ግብረ-ኃይሉ በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 13 ንዑስ ቁጥር 6/ሀ መሰረት የራሱን የባንክ አካዉንት ይከፍታል፡፡

ለ/ የባንክ ሂሳቡ በግብረ-ኃይሉ ስብሳቢ/በስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ኃላፊና በሂሳብ ሹሙ ፊርማ ብቻ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

ሐ/ የገንዘብ ሂሳብ አሰራሩ በመደበኛዉ የጥንድ ሂሳብ (Double entry) የሚሰራ ይሆናል፡

14) የግብረ ሀይሉን ሂሳብ ኦዲት ስለማድረግ

ሀ/ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኦዲት መምሪያ በሚኒስትሩ ትእዛዝ፣ ወይም በግብረሀይሉ ጥያቄ ወይም በራሱ ተነሳሽነት የግብረ-ሀይሉን አጠቃላይ ሂሳብ ይመረምራል፣ ዉጤቱን ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡፡

ለ/ በዉጤቱም መሰረት ተገቢዉ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

## ክፍል ፮

## 13. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ

በኤች.አይ.ቪ. ምክንያት ታማሚ ለሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ወላጅ አልባ ለሆኑ ሌሎች ህፃናት አቅም በፈቀደ መጠን ቁሳዊና ሞራላዊ እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ ቫይረሱን ከመዋጋት አንጻር ከፍተኛ አወንታዊ ጎን ያለዉ በመሆኑ ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ ይገባል፡፡ ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረገዉም የሚከተሉትን ነጥቦች እና በተራ ቁጥር 17 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

1) ድጋፍና እንክብካቤ የሚጠይቁ ሠራተኞች (ቤተሰቦቻቸው) የድጋፍ ጥያቄአቸውን ሊያቀርቡ የሚችሉበት ግልጽ አሰራር መዘርጋት፣ በየጊዜዉም እየፈተሹ ማሻሻል፣

2) ድጋፍና እንክብካቤ የሚጠይቁ ሠራተኞችን (ቤተሰቦቻቸውን) የችግር ዓይነትና መጠን በማስረጃ በተደገፈ መልኩ ማጣራትና መለየት፣

3) ለድጋፍና እንክብካቤ የተለዩ ሠራተኞችን /ቤተሰቦቻቸዉ/ እንደችግራቸዉ አጣዳፊነትና ክብደት ከአድሎ በጸዳ መልኩ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣

4) የድጋፍና እንክብካቤ ዓላማው ይሳካ ዘንድ ድጋፉን በቀጥታ ለተረጂዉ /ለተጎጂዉ/ ሰዉ ወይም ሰዎች እንዲደርስ ማድረግ ወይም መስጠት፣

5) በተደረገዉ እንክብካቤና ድጋፍ ተረጂዉ ወገን ምን ያህል በአግባቡ እንደተጠቀመበት እና ከዚህም ጋር በተያያዘ ድጋፍና እንክብካቤዉ እያመጣ ያለዉን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ዉጤት መገምገምና ተገቢዉን መረጃ መያዝ፣

6) ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸዉ ወገኖች የተረጂነት ስሜት አድሮባቸው የሰዉ እጅ ጠባቂ እንዳይሆኑ፣ እንደአስፈላጊነቱ ደረጃ በደረጃ ከተረጂነት ተላቀዉ የራሳቸዉ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸዉ ከሌሎች አጋሮች ጋር በመሆን ተገቢዉን ጥረት ማድረግ፣

7. ለድጋፍና እንክብካቤ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሚሰበሰበው የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ለታቀደለት ዓላማ ብቻ በአግባቡ ይዉሉ ዘንድ በግልጽነትና በተጠያቂነት መርህ ላይ በመመስረት በቁጠባ መጠቀም፣

8) እንደ አስፈላጊነቱ የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጡን ሊያግዙ የሚችሉ ሌሎች አዎንታዊና ጤናማ አካሄዶችን መከተልና ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

## 14. ለድጋፍና እንክብካቤ ብቁ ስለመሆን

የኤድስ ህመምተኛ የሆነ የመ/ቤቱ ሠራተኛ ወይም ሠራተኛው ከሞተ በኋላ ቤተሰቦቹ ሊረዱ የሚችሉት የገቢ መጠናቸዉና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸዉ በአግባቡ ተጠንቶና የችግራቸዉ መጠንና አንገብጋቢነት ታይቶ እንደየቅደም ተከተላቸዉ ቅድሚያ በመስጠት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ድጋፍ የሚሰጠዉ:-

1) **የኤድስ ሕመምተኛ ለሆኑ ሠራተኞች፤** ቫይረሱ በደሙ ዉስጥ የሚገኝ ሠራተኛ በተለያዩ የጤና ችግሮች የተነሳ የኤድስ ህመምተኛ መሆኑ በምርመራ ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

2) **በኤች.አይ.ቭ/ኤድስ ሳቢያ የመ/ቤቱ ሰራተኛ በሞት ሲለይ/ስትለይ ለቤተሰብ፤** ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ወይም ቤተሰቦች ሌላ ለመኖር የሚያስችላቸዉ የገቢ ምንጭ የሌላቸዉ በመሆኑ ምክንያት ለዕለታዊ የኑሮ ችግር የተጋለጡ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

3) በቁጥር ለተወሰኑ ወላጅ አልባ ህፃናት፣

## 15. የድጋፍና እንክብካቤ ጥያቄ አቀራረብ

በቫይረሱ ምክንያት ህመምተኛ የሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸዉ ድጋፍ ሲያገኙ የሚችሉት ጥያቄያቸዉን በፅሁፍ አድርገዉ ከተገቢዉ ማስረጃ ጋር ለጸረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግብረኃይል ሰብሳቢ/ለስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ኃላፊ ሲያቀርቡ ብቻ ይሆናል። ለዚህም፡-

1) ድጋፍና እንክብካቤ ጠያቂዉ ሠራተኛ ሊደረግለት የሚፈለገዉን የድጋፍና እንክብካቤ አይነት የሚገልጽ የጽሁፍ ማመልከቻ በግንባር ወይም በሚወክለዉ ሰው አማካኝነት ለግብረ-ሀይሉ ሰብሳቢ/ለስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡
2) ከድጋፍ ጥያቄዉ ማመልከቻ ጋር አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ዋና እና ፎቶ ኮፒ ተያይዘዉ መቅረብ አለባቸዉ። የማስረጃዎቹ ትክክለኛነት ከተረጋገጠ በኋላ ዋናዎቹ ለባለጉዳዩ የሚመለሱ ይሆናል።
3) በቃል የሚቀርቡ የድጋፍና እንክብካቤ ጥያቄዎች ተቀባይነት የላቸዉም።

## 16. የድጋፍ አሰጣጥ መስፈርቶች

1) የድጋፍ ጠያቂዉ የገቢ መጠን፣
2) ያለበት የጤንነት ሁኔታና የሃኪም አስተያየት፣
3) የቤተሰብ ሁኔታና ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ብዛት፣
4) ከሌሎች ድጋፍ አድራጊ ተቋማት የሚያገኘዉ ድጋፍ ካለ አይነትና መጠን፣
5) ከተረጂዉ አንጻር መሠረታዊና አስፈላጊ ተብለዉ ሊወሰዱ የሚችሉ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

## 17. የድጋፍና እንክብካቤ አይነቶች

ከላይ በተራ ቁጥር 15 እና 17 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ በቫይረሱ ምክንያት ህመምተኛ የሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞች፣

1) ለጤናቸዉ ተስማሚ በሆነ የሥራ አካባቢ እንዲሰሩ ማድረግ፣
2) የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸትና ተጠቃሚ ማድረግ፣
3) የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣
4) እንደአስፈላጊነቱ የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣

## 18. በገንዘብ የሚደረግ ድጋፍ

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ድጋፍ ፈንድ በጊዜም ሆነ በመጠን የሚያደርገዉ የገንዘብ ወይም የአይነት ድጋፍ ከሰራተኛው መዋጮ

እና ከሌሎች በሚያገኘዉ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍና ዕርዳታ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ድጋፉ እንደገቢዉ ሁኔታ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡ በመሆኑም፡-

1) በቫይረሱ ምክንያት ህመምተኛ የሆነና ቤተሰብ የመሰረተ ሠራተኛ ድጋፍ በጠየቀ ጊዜ በወር የ300.00 ብር (ሦስት መቶ ብር) ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ አቅም በፈቀደ መጠን ተጨማሪ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2) ድጋፍ ጠያቂዉ ሠራተኛ በሕይወት እያለ ቤተሰብ ያልመሰረተና የሚያስተዳድራቸዉ አረጋዉያን ካሉ በወር ብር 200.00፣
3) ቤተሰብ መስርቶ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ለተለየ ሠራተኛ:-

ሀ/ ከ1-4 ለሚሆኑ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ለእያንዳንዳቸዉ በወር ብር 100.00፣

ለ/ ከ4 በላይ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በድምሩ በወር ብር 500.00፣

ሐ/ የሟች ሕጋዊ የትዳር ጓደኛ ምንም የገቢ ምንጭ የሌለዉ/የሌላት ከሆነ/ከሆነች በወር ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

4) ወላጅ አልባ የሆኑ ሌሎች ህፃናት ግብረ-ኃይሉ በሚወስነው መሠረት የሚረዱ ይሆናል፡፡
5) ግብረ-ኃይሉ የገቢ መጠኑን መሠረት በማድረግ ለተረጂዎች ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግበትን ሁኔታ በየወቅቱ እየተወያየ በመወሰን ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡፡
6) ግብረ-ኃይሉ በዓይነት ድጋፍ ሊያደርግ የሚችልበት ሁኔታና አቅም ካገኘ ከገንዘብ ድጋፍ ጋር በተመጣጠነ መልኩ የዓይነት ድጋፍ ማድረግን በተመለከተ፣ እንደሁኔታዉ ተወያይቶ የሚወስነዉ ይሆናል፡፡

## 19. ድጋፍና እንክብካቤ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

1) ድጋፍ የሚደረግለት ሠራተኛ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይና ቤተሰብ የሌለዉ ከሆነ፣
2) ድጋፍ የሚደረግለት ሠራተኛ የተሻለ የገቢ ምንጭ ወይም ድጋፍ በቋሚነት የሚያገኝበት ሁኔታ ሲፈጠርና ይህም በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፣
3) ይረዱ የነበሩ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ዕድሜያቸው 18 ዓመት መድረሱ ሲረጋገጥ፣
4) ይረዱ የነበሩ አረጋዉያን ወላጆች፣ ባል/ሚስት በሞት ከተለዩ፣
5) ድጋፍ የሚደረግለት ሠራተኛ ወይም ቤተሰቡ፣ የሚደረግለትን የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ለታቀደለት ዓላማ ከማዋል ይልቅ ከዓላማዉ ተጻራሪ ለሆነ እና ችግሩን ሊያባብስ በሚችል ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚያዉል መሆኑ በማስረጃ በተደገፈ ሁኔታ ሲቀርብና በግብረሀይሉ ሲታመንበት ይሆናል፡፡

## ክፍል ፮

## የዲሲፕሊንና ቅሬታ ሥርዓቶች

### 20. የዲሲፕሊን ጥፋት

1) የሥራ ቦታዎችን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለመከላከልና አድሎአዊ አሠራሮችን ለማስቀረት እንዲቻል በመ/ቤቱ ሥራ ቦታ ላይ ኤች.አይ.ቪን ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ድርጊቶች እንዲሁም ማንኛቸዉም አድሎአዊ አሠራሮች ሰብአዊ መብትን የሚጥሱ ተግባራት በመሆናቸዉ የሥራ ቦታ ጥፋቶች ናቸዉ፤

2) ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ተያይዘዉ የሚፈጸሙ ጥፋቶች በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 68 ላይ ከተደነገጉት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ጋር እኩል ክብደት ያላቸዉ ጥፋቶች ናቸዉ፤

3) በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መ/ቤቶች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ላይ በተቀመጠዉ መሰረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታዎች በማናቸዉም ሁኔታ ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ኤች.አይ.ቪን ለማስተላለፍ የሚደረጉ ድርጊቶችን መፈጸም በከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስቀጣ ተግባር ነዉ፡፡

4) በመደበኛ ስራዎች ላይ እንዲሁም ቅጥር፣ እድገትና ዝዉዉር በማስታከክ በሴቶች ላይ ፆታዊ ጥቃት መፈጸም ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ነዉ፡፡

5) በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ለሚገኝ እና ለኤድስ ሕሙማን ሰራተኞች የተረጋገጡላቸዉን መብቶች ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት መጣስ በከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስቀጣ ተግባር ነዉ፡፡

### 21. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቶች

1) ከኤችአይቪ/ኤድስ ጋር የተያያዙ ጥፋቶች ወይም አድሎአዊ አሠራሮች የተፈጸመባቸዉ ሠራተኞች አቤቱታቸዉን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የማቅረብና የተሰጠዉን ምላሽ በጽሁፍ የማወቅ መብት አላቸዉ፡፡

2) የመ/ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴም ድርጊቱ መፈጸሙን ካመነ በአጥፊዉ ሠራተኛ ወይንም ኃላፊ ላይ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 68/14 መሠረት የዲሲፕሊን ክስ እንዲቀርብ ጉዳዩን ለመ/ቤቱ የአስተዳደር አካል ወይም ሕግ አገልግሎት ይመራል፣ በዲስፕሊን ተጣርቶ ሲቀርብለትም ዉሣኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ፰

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 22. መመሪያዉ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ይህ መመሪያ ሻይረሱ በህክምና ረገድ በሚኖረዉ ለዉጥ እንዲሁም በየጊዜዉ የሚወጡ ሕጐችን እና ሌሎች ገዥ/ወሳኝ ጉዳዮችን ግምት ዉስጥ በማስገባት እንደ አስፈላጊነቱ የሚሻሻል ይሆናል።

### 23. መመሪያዉን ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይህንን መመሪያ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸዉ።

### 24. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሰኔ 27 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር

12/2004

# የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

12/2004

# የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ቁጥር 12/2004

ሰኔ 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ


መ ግ ቢ ያ .................................................. 1

**ክፍል ፩**

1. አጭር ርዕስ .................................................. 2
2. ትርጓሜ .................................................. 2
3. የመመሪያው ዓላማ... .................................................. 4
4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን... .................................................. 5

**ክፍል ፪**

5. መመሪያው የሚያራምዳቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች .................................................. 5
6. የመመሪያው ቁልፍ መርሆዎች .................................................. 6

**ክፍል ፫**

7. የመመሪያው አጠቃላይ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች .................................................. 9

**ክፍል ፬**

8. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር ሥልጣንና ተግባራት .................................................. 10
9. የመ/ቤቱ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት .................................................. 12
10. ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት .................................................. 13

**ክፍል ፭**

11. ግብረ-ኃይል ስለማቋቋም .................................................. 14
12. የግብረ-ኃይሉ አደረጃጀት .................................................. 14

**ክፍል ፮**

13. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ .................................................. 19
14. ለድጋፍና እንክብካቤ ብቁ ስለመሆን .................................................. 20
15. የድጋፍና እንክብካቤ ጥያቄ አቀራረብ .................................................. 21
16. የድጋፍ አሰጣጥ መስፈርቶች .................................................. 21
17. የድጋፍና እንክብካቤ ዓይነቶች .................................................. 21
18. በገንዘብ የሚደረግ ድጋፍ .................................................. 21
19. ድጋፍና እንክብካቤ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ .................................................. 22

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development and Construction

8100/ም/34
30/4/2009

ለሥርዓተ ፆታ ሚይንስትሪሚንግ መምሪያ
ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡- የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፣

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥር በሚገኙ ሁሉም ቢሮዎች እና ጽ/ቤቶች ተፈጻሚ የሚሆነውን የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ቁጥር 16/2004 ሆኖ ከሰኔ 2004 ዓ.ም. ጀምሮ የፀደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት የመመሪያውን አፈጻጸም እንድትከታተሉ የፀደቀው 1 ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጐ የተላከ መሆኑን እየገለጽን የሀነዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም እንድታስፈጽሙት እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የኮንስትራክሽን ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና የሚኒ-ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ
- ለከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮ
- ለመሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ ኤጀንሲ
- ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ
- ለከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ቢሮ
- ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
- ለመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመ የመንግሥት ሕንፃዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ
- ለድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ
- ለሕዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት
- ለተቀናጀ የመሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽ/ቤት
- ለኦዲት መምሪያ
- ለሕግ መምሪያ

ከ/ል/ኮ/ሚ/ር
ከአንድ ጥራዝ አባሪ ጋር

**ክፍል ፱**

20. የዲሲፕሊን ጥፋት .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ... ... 23

21. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቶች .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ... ... 23

**ክፍል ፲**

22. መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ..... 24

23. መመሪያውን ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ......... 24

24. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ....... 24

## መ ግ ቢ ያ

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት የዓለማችን ከፍተኛ ችግር ከሆነ ውሎ አድሯል። እያስከተለ ያለው ችግርም ከጤና ችግር በላይ በመሆን የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የፖለቲካዊ ቀውሶችን አስከትሏል፤ በማስከተል ላይም ይገኛል። አገራችን ኢትዮጵያ ከድህነት ለመውጣት፣ ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥና መልካም አስተዳደርን ለመገንባት የምታደርገውን ጥረት እየተፈታተነም ነው። ቫይረሱ እያስከተለ ያለው ሰብዓዊ ጉዳት አስከፊ ከመሆኑም በተጨማሪ መ/ቤቶች የሰለጠነ ባለሙያ እንዲያጡ፤ ሥራ ያልተሰራባቸው መደበኛ የሥራ ቀናት እንዲበዙ፤ ተተኪ የሰው ኃይል ለማሰልጠን የሚያስፈልግ ተጨማሪ ወጪ እንዲያድግ፤ የተቋማት የሕክምና፣ የካሣ ክፍያና የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ እንዲጎር፤ በአጠቃላይ የተቋማት የሥራ ውጤትና ትርፋማነት እያሽቆለቆለ እንዲሄድ ተፅዕኖ በማድረግ በሀገሪቱ አጠቃላይ ልማትና እድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል።

መንግስት የወረርሽኙን ስርጭት ለመግታትና እያስከተለ ያለውን ፈርጀ ብዙ ጉዳት ለመቀነስ በተቀናጀ ሁኔታ ለመቆጣጠርና ለመከላከል ይቻል ዘንድ ብሔራዊ ፖሊሲ በማውጣት እና ይህንንም ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ ህብረተሰቡንና የልማት አጋሮችን ያሳተፉ በርካታ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። እነዚህን ጥረቶች ይበልጥ አጠናክሮ ውጤታማ ለመሆን፣ በሥራ ቦታዎች የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ወጥነት ያላቸውና በሀገራዊው የጤና ፖሊሲ መርሆዎች ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ በተደረገው እንቅስቃሴ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ በሴክተሮችና በተቋማት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መመሪያዎች በመቅረጽ ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴርም ይህንኑ ሁኔታ አጠናክሮ በመቀጠል ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ሠራተኞች ተገቢውን ትኩረት ለመስጠትና የኤድስ ህመምተኛ ለሆኑት ደግሞ አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ ለማድረግ፣ በሀገራዊው የጤና ፖሊሲ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ አዘጋጅቷል ። ይህ መመሪያ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መ/ቤቶች የስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲችሉ በወጣዉ መመሪያ አራት ተራ ቁጥር 4.1 መሰረት ተዘጋጅቷል።

## ክፍል ፩

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የስራ ቦታ የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ቁጥር 16/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

ስቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፣

1) **"ሚኒስቴር መ/ቤት"** ማለት፡- በአዋጅ ቁጥር 691/2003 የተቋቋመው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነዉ፡፡
2) **"ሠራተኛ"** ማለት፡- በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰዉ ነዉ፡፡
3) **"የበላይ አመራር"** ማለት፡- የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር እና ሚኒስትር ዴኤታ ወይም እንደ አግባቡ ሌሎች የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችን ያመለክታል፡፡
4) **"የሥራ ቦታ"** ማለት፡- የመ/ቤቱ ሠራተኞች ሥራቸዉን የሚያከናዉኑበት መደበኛ ስፍራ ነዉ፡፡
5) **"ኤች.አይ.ቪ"** ማለት፡- ሰዉነት በተፈጥሮ በሽታን ለመቋቋምና ለመከላከል ያለዉን ችሎታ ወይም ብቃት የሚሸረሽርና ደረጃ በደረጃም ለበሽታዉ ወይም ለኢንፌክሽን የሚዳርግ ተህዋስ ነዉ፡፡
6) **"ኤድስ"** ማለት፡- በኤች.አይ.ቪ ሳቢያ ሰዉነት በተፈጥሮ ያለዉን በሽታን የመከላከል አቅም በማዳከም በማንኛዉም ተደራራቢ ኢንፌክሽን ከተያዘ በኋላ የሚከሰት የበሽታ መገለጫ ነዉ፡፡
7) **"ኤች.አይ.ቪ በደሙ ውስጥ ያለበት ሰው"** ማለት፡- አግባብ ካለዉ ባለስልጣን መ/ቤት ፈቃድ ባገኘ የምርመራ ተቋም የግለሰቡ የደም ናሙና ተወስዶ ደረጃዉን በጠበቀ የምርመራ ሂደት ቫይረሱ በደሙ ዉስጥ ስለመኖሩ የተረጋገጠ ግለሰብ ነዉ፡፡
8) **"የኤድስ ህመምተኛ"** ማለት፡- በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ሳቢያ ሰውነቱ በተፈጥሮ ያለው በሽታን የመከላከል ችሎታ መዳከም የተነሳ በሚከሰቱ የተለያዩ በሽታዎች የተያዘ ህመምተኛ ሰው ነው፡፡

9) **"ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናት"** ማለት፡- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኛ ከነበሩ ሰው/ሰዎች ተወልደው በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ አንድ ወይም ሁለቱንም ወላጆቻቸውን ያጡ ዕድሜአቸዉ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት ናቸው።

10) **"የኤች.አይ.ቪ. የደም ምርመራ"** ማለት፡- በደም ውስጥ ኤች.አይ.ቪ. መኖር ወይም አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚደረግ ደረጃውን የጠበቀ የደም ምርመራ ሂደት ነው።

11) **"ቅድመ ምርመራ የምክር አገልግሎት"** ማለት፡- ለኤች.አይ.ቪ. የደም ምርመራ በፈቃደኝነት የቀረበ ሠራተኛ ምርመራ ከማድረጉ በፊት ለምርመራው የተነሳሳበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ የምርመራዉ ዉጤት በቀጣይ ሕይወቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያስከትል ተመርማሪው ሥነ-ልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርግ የሚረዳ የባለሙያ ምክር ነው።

12) **"ድህረ ምርመራ የምክር አገልግሎት"** ማለት፡- በፈቃደኝነት የኤች.አይ.ቪ. ደም ምርመራ ላደረገ ሠራተኛ የደም ምርመራ ዉጤቱን መሠረት በማድረግ በባለሙያ የሚሰጥ የምክርና የሥነ-ልቦና ድጋፍ ነዉ።

13) **"የአባለዘር በሽታ"** ማለት፡- በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ወቅት ከአንዱ ሰዉ ወደ ሌላዉ ሰዉ በረቂቅ ህዋስ ወይም ጀርም አማካኝነት የሚተላለፍ ኢንፌክሽን/በሽታ ሲሆን፤ ጨብጥን፣ ከርክርን፣ ባምቡሌን፣ ቂጥኝን፣ ያካትታል።

14) **"ኮንዶም"** ማለት፡- በወንድ ብልት ላይ ወይም በሴት ብልት ዉስጥ የሚጠለቅ ቅባትነት ያለዉ ፕላስቲክ ሲሆን፤ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ወቅት ኤች.አይ.ቪ. ቫይረስን ጨምሮ ሌሎች የአባላዘር ተዋህስያንና ያልተፈለገ እርግዝናን የመከላከል ዕድል እንዲሰፋ የሚረዳ ነዉ።

15) **"ግብረ-ኃይል"** ማለት፡- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስተባብርና የሚሰራ የአባላት ስብስብ/ግብረ-ኃይል ነው።

16) **"ድጋፍና እንክብካቤ"** ማለት፡- ቫይረሱ በደማቸዉ ውስጥ የሚገኝ እና ህሙማን ሠራተኞች እንዲሁም ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናት የተሻለ አኗኗር እንዲኖራቸዉ እና ወረርሽኙንም በመቀነስ ረገድ የበኩላቸዉን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ የሚያግዝ ሰብአዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባር ነዉ።

17) **"ምስጢር"** ማለት፡- የአንድ ሰዉ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ዉጤት ወይም የህመም ሁኔታ ከኤድስ ጋር ያለዉን ዝምድና የተመለከተ የሕክምና ሪኮርድ ወይም መረጃ በሚስጥር የሚያዝበትና ይፋ የማይወጣበት የአሰራር ሥርዓት ነዉ።

18) **"የመከላከል ተግባር"** ማለት፡- መንስኤዉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሆነ የአንድ የጤና ችግር ወይም በሽታ የሚያስከትል ተህዋስ እንዳይዛመት ተገቢ ጥንቃቄ የማድረግ ተግባር ሲሆን፤ በሽታዉን ለመከላከል የሚደረግን ማንኛዉም የማስተማርና ሌሎች ተግባሮችን ያካትታል።

19) **"መቆጣጠር"** ማለት፡- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት እና ሊያስከትል የሚችለዉን ጉዳት ለመቀነስና ባለበት ለማቆም የሚወሰድ እርምጃ ማለት ነዉ፡፡

20) **"ምቹ የስራ ሁኔታ መፍጠር"** ማለት፡- አንድ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኛ ቫይረሱ በደሙ ውስጥ መኖሩ በምርመራ ሲረጋገጥ ወይም ለሠራተኞች ሲገለጽ የተመደበበት የሥራ ክፍል ከአካላዊና ከአእምሮአዊ የጤና ሁኔታዎች ጋር የተመቻቸ እንዲሆን ጥረት የማድረግ ወይም ወደ አመቺ ሥራ ማዛወር ወይም ሌሎች ተገቢ አስተዳደራዊ ድጋፎችን ማድረግ ነዉ፡፡

21) **"መረጃ"** ማለት፡- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ በሁሉም ዘንድ በግልጽ ሊታወቅ የሚገባ አሃዛዊ ጥንቅር ወይም ድፍን ንጽጽራዊ ትንታኔ የያዘ ወቅታዊ ዘገባ ነዉ፡፡

22) **"ትምህርታዊ ፕሮግራም"** ማለት፡- በተደራጀ መልክ መልእክትን ለሚመለከተዉ አድማጭ ወይም ተመልካች በተጠና ዉጤታማ የማስተላለፊያ መንገድ መግለጽ ነዉ፡፡

23) **"ጥናትና ምርምር"** ማለት፡- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ላይ የተገኘ ዕዉቀት፣ ሳይንሳዊ መረጃ፣ ግኝትና የነጠረ ሃሳብን ወዘተ... ለሌሎች ዉጤታማ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ ወይም በዚህ መነሻነት ተጨማሪ ዕዉቀትና ሃሣብ ለማግኘት የሚካሄድ ጥናት ነዉ፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

የመመሪያዉ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡-

1) በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፤

2) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በስራ ቦታዎች ያለዉን አሉታዊ ተፅዕኖ በሚመለከት ግንዛቤ በማሳደግ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለዉጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ተግባራትን ለማካሄድ፣

3) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሠራተኞች፣ በቤተሰቦቻቸዉ እንዲሁም በዘርፉ እና መ/ቤቱ እያደረሰ ያለዉን አሉታዊ ተፅዕኖ በመከላከል ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ጥረት ለማድረግ፣

4) በቫይረሱ ምክንያት ሕሙማን ለሆኑ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች እንዲሁም በበሽታዉ ሳቢያ በሞት ለተለዩ የመ/ቤቱ ባልደረቦች ቤተሰቦች እንደአስፈላጊነቱና አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፍና እገዛ ለማድረግ፣

5) ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ህሙማን የሆኑ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች መድልዎ የማይፈጸምባቸው፤ ሰብዓዊ መብታቸው የተከበረ፤ ተገቢው ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ፤

6) በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ለአካለመጠን ያልደረሱ ህጻናት ልጆችና በአጠቃላይ ተጠቂ የህብረተሰብ ክፍሎች አቅም በፈቀደ መጠን የምግብ፣ የአልባሳት፣ የትምህርትና የጤና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሥራ አካባቢዎችና በሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ፪

# የመመሪያው ስትራቴጂክ ጉዳዮች እና መርሆዎች

## 5. መመሪያው የሚያራምዳቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች

### 1) ዘርፈ ብዙነት

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ያልነካው የሕብረተሰብ ክፍልና ተፅዕኖ ያላሳደረበት የኢኮኖሚ ሴክተር የለም፡፡ ስለሆነም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከናወኑ ማናቸውም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራሞች ሠራተኛውን ጨምሮ ሁሉንም የልማት አጋሮች ያቀፉና ንቁ ተሳትፎን ያረጋገጡ ሊሆን ይገባል፡፡ የሥራ ቦታዎችም ወረርሽኙን የመከላከል ተግባርን እንደመደበኛ ተግባር በመውሰድ ምላሽ መስጠት ይገባቸዋል፡፡

### 2) ባለቤትነት

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስመግታትም ሆነ የሚያስከትለውን ተፅዕና ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ የሚቻለው በሥራ ቦታዎች በባለቤትነትና በኃላፊነት የመንቀሳቀስ ስሜት ሲኖር ነው፡፡ ስለሆነም የወረርሽኙን የአውዳሚነት ባህሪ በወል በመረዳት፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያውን እንደአስፈላጊነቱ በማሻሻል፣ የአፈጻጸም መመሪያዎችን በማዘጋጀት፣ ፈጻሚ አካላትን በማደራጀት፣ ዕቅድ በመንደፍ፣ በጀት በመያዝ፣ የአፈጻጸም መርሐግብር በማመላከትና የክትትልና የግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

### 3) ፈጣንና የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ማድረግ

ወረርሽኙ እስካሁን በሀገር ላይ ያደረሰው ጉዳት እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡ ስለሆነም በሀገሪቱ በሁሉም መስኮች የሚካሄደው የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዘመቻ አስቸኳይና የሁሉም የጋራ ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር ሚኒስቴር መ/ቤቱም በፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ትግሉ ውስጥ ፈጣንና የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ፈጥሮ ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡

4) የስርዓተ ፆታ እኩልነት መብትን ማራመድ

ማንኛውም በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ላይ የሚደረግ እንቅስቃሴ ፆታ ተኮር ሊሆን ይገባል፡፡ በተጓዳኝም በሥራ ቦታ በሚካሄዱ የመከላከል፣ የድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት ሴቶችን እና ወጣቶችን በንቃት ማሳተፍ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

5) ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ከሚገኝ ወገኖች ጋር ይበልጥ መተባበር

ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ወገኖች ከግልና ከማኀበራዊ ልምዳቸው በመነሳት፣ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለማስተማር ከፍተኛ አቅምና ብቃት አላቸው፡፡ የምክር አገልግሎት፣ ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ለመስጠትም መሰልጠን ይችላሉ፡፡ ከዚህ አኳያ በሥራ ቦታዎች የሚካሄዱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከል እንቅስቃሴዎች በእነዚህ ወገኖች የነቃ ተሳትፎ ሊታገዝ ይገባል፡፡ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ወገኖችን በፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ማሣተፍ የቫይረሱን ስርጭት ለመቀነስና የእነሱንም ሕይወት ለማሻሻል አስተዋፅዖ እንዳለው መገንዘብ ይገባል፡፡

6) ውጤታማነት

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት ልማትን እና የእድገት ውጤቶችን የመሸርሸር ጫና ከማሳደሩም በተጨማሪ ያለንን ውስን ጥሪት በልማት ላይ እንዳናውል ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ወረርሽኙን ለመዋጋት የሚደረገው እንቅስቃሴ ውጤታማ ይሆን ዘንድ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የተላበሰ አሠራር የማስፈን ጥረት ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡

7) አግባብ ያለው የሀብት አጠቃቀም

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ድህነት ስር እንዲሰድና እንዲባባስ ያደርጋል፡፡ በአፀፋውም ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭነትን ያሳድጋል፡፡ ወረርሽኙን ለመግታት የሚደረገው እንቅስቃሴ ሀገራዊ ሀብትን በአግባቡና በወቅቱ የመጠቀም ጥረትን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም በስራ ቦታ የሚካሄዱ ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎች የራስ ሀብትን በመፍጠርና በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል መርህ ላይ ተመርስተው ሊካሄዱ ይገባል፡፡

## 6. <u>የመመሪያዉ ቁልፍ መርሆዎች</u>

1) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሥራ ቦታ ጉዳይም መሆኑን መቀበል፤

የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሥራ ቦታዎችና አጠቃላይ አገራዊ የልማት ችግር መሆኑን በመቀበል፣ ወረርሽኙ በመስሪያ ቤቱ ተልዕኮ አፈጻጸምና በሠራተኞች ኑሮ ላይ የሚያስከትለውን ፈርጀ ብዙ ተጽዕና ለመቋቋም በባለቤትነት ስሜትና በቁርጠኝነት ይንቀሳቀሳሉ፡፡

2) በሥራ ቦታ መድልዎና ልዩነት አለማድረግ፤

የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞችና ሥራ ፈላጊ አመልካቾች ምንም ዓይነት መድልዎና መገለል አይደረግባቸውም።

3) በሥራ ቦታዎች ለሥርዓተ ፆታ እኩልነት እና ልዩ ትኩረት ለሚሹ ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት፤

ሀ/ መ/ቤቱ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን እና ሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚነድፈው ማንኛውም ፕሮግራም በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መርህ ላይ የተመሰረተ እና የሴቶችን ተሳታፊነት የሚያጎለብት ይሆናል።

ለ/ በተፈጥሯዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮች ምክንያት ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ወጣት ሠራተኞች እና የሥራ ባህሪዎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

4) ጤናማና ምቹ የሥራ አካባቢ የመፍጠር ጥረትን ማጠናከር፤

የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ፕሮግራሞችን በመንደፍና በመተግበር የመስሪያ ቤቱ የሥራ ቦታዎች ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭትና ሌሎች የጤና ጠንቆች ሥጋት የፀዱ ምቹና ጤናማ እንዲሆኑ ይደረጋል።

5) የውይይት፣ የምክክርና የድርድር ባሕል ማዳበር፤

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሠራተኞች እና በሌሎች አጋር ድርጅቶች መካከል በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ በቅን ልቦናና በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረተ ወቅታዊ ውይይትና ምክክር ሊደረግ ይገባል።

6) የኤች.አይ.ቪ በደም ውስጥ መኖር ለሥራ ቅጥርና የሥራ ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እንደ ብቃት መስፈርት እንዳይወሰድ ተገቢውን ጥረት ማድረግ፤

ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራን ሊያስገድዱ አይገባም። ነባር ሠራተኞችም ከሥራቸው ባህሪ አኳያ የሚያደርጓቸው የጤና ምርመራዎች አስገዳጅ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራን አለማካተታቸውን መረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

7) የሠራተኞች የግል የጤና መረጃ በሚስጥር መያዝ እና ሚስጥር መጠበቅ፤

ሥራ አመልካቾችም ሆኑ ነባር ሠራተኞች ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የተያያዙ የግል የጤና መረጃዎችን ያለፈቃዳቸው እንዲገልጹ ማስገደድ ተቀባይነት አይኖረውም። የሠራተኞች የግል የጤና መረጃ በሚስጥር የሚያዝና ያለተመርማሪው የጽሑፍ ፈቃድ

ወይም አግባብ ያለው አካል በሚያቀርበው ህጋዊ ጥያቄ ካልሆነ በቀር ለሌላ ሶስተኛ አካል የማይገለጽ መረጃ ነው። በተመሣሣይ ሁኔታም ሠራተኞች ስለ ባልደረቦቻቸው ይህንን የመሰለ የግል የጤና መረጃ እንዲያሳውቁ ማስገደድ ሰብዓዊ መብትን የጣሰ ድርጊት ሆኖ ይወሰዳል። በሚ/ር መ/ቤቱ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራ ውጤትን ጨምሮ የሠራተኞች የግል የጤና መረጃ በሚስጥር ሊጠበቅ ይገባል።

8) በኤች.አይ.ቪ ምክንያት የሥራ ውል እንዳይቋረጥ ማድረግ፤

በማንኛውም ሁኔታ የኤች.አይ.ቪ በደም ውስጥ መኖር የሥራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አይሆንም። እንደ ሌሎች በሽታዎች ሁሉ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በሽታዎች ሕመምተኛ የሆኑ ሠራተኞች የጤና አቋማቸው ሥራ እንዲሰሩ ብቁ የሚያደርጋቸው እስከሆነ ድረስ በተመደቡበትና ባሉት ሌሎች ተስማሚ የሥራ መደቦች ላይ ተዘዋውረው የመስራት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

9) ወረርሽኙን በጋራና በቅንጅት መከላከል፤

ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍልና የልማት አጋሮችን በቅንጅት ያሳተፈና ቁርጠኛ አመራር ያለው ሀገራዊ ፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ውጤታማ መሆኑን ተሞክሮዎች ያስረዳሉ። ስለሆነም የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት በብሔራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች የተጠቀሱ የመከላከያ እርምጃዎች በሥራ ቦታዎች ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል።

በሥራ ቦታዎች ወረርሽኙን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ በዕቅድ የተደገፈ ሆኖ ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ሊደረግበት ይገባል። ይህ ዓይነቱ በሥራ ቦታዎች ወረርሽኙን የመከላከል ዘርፈ ብዙ ሥራ ወቅታዊ መረጃ፣ ትምህርት እና የባህሪ ለውጥ ተግባራትን፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የምክርና የደም ምርመራን፣ የተዛማጅ ሕመሞችን ህክምናን፣ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል ሥራን፣ የፀረ-ቫይረስ መድኃኒት አገልግሎትን፣ የአባለዘር በሽታዎችን የማከም ሥራን፣ የፆታ እኩልነት ከልማት ሥራዎች ጋር አካትቶ ተፈፃሚ ማድረግን፣ የሥራ ላይ መብቶች ጥበቃን፣ ጥናትና ምርምር ማድረግን፣ የሥራ አካባቢ ንፅህና መጠበቅን፣ ጤናማና ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠርን፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያዎችን ማውጣትና አስፈጻሚ ግብረ ሀይል ማደራጀትን፣ የኤድስ ፈንድን ማቋቋም፣ በጀት መያዝን፣ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት መዘርጋትን፣ በጉዳዩ ዙሪያ ከሌሎች አጋሮች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነትና ትብብር በማድረግ አቅም መገንባትን ...ወዘተ. ሊያካትት ይገባል።

10) በሥራ ቦታዎች ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣

ድጋፍ እና እንክብካቤ በሥራው ዓለም ለሚካሄድ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምላሽ ፈር ቀዳጅ ዕርምጃዎች ናቸው፡፡ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ሰዎችን ጨምሮ ሁሉም ሠራተኞች ሕግ ወይም የአስተዳደር ደንብ በሚፈቅደው መሠረት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞችን የመጠቀም፣ ጥቅማ ጥቅሞችን የማግኘት፣ የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች ተጠቃሚ የመሆን እና ተገቢ የሆነ አስተዳደራዊ ድጋፍና እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

ቫይረሱ በደማቸው በመኖሩ ምክንያት ተደጋጋሚ ሕመም የሚያጋጥማቸው ሠራተኞች የተራዘመ የሕክምና ፈቃድ እንዲያገኙ ማድረግን፣ የጤና አቋማቸውን ባገናዘበ መልኩ ጥቅማቸው ሳይጓደል ወደ ቀላል ሥራ የመዛወር ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል፡፡ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ በሥራ ቦታዎች ለሠራተኞች የሚሰጡ የሕክምና፣ የድጋፍና እንክብካቤ ፕሮግራሞች (የጤና ክትትል፣ እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ ድጋፎች) በዋነኛነት በሠራተኛው የጋራ ስምምነት በሚዋጣ ወርሀዊ የኤድስ ፈንድ ላይ የተመሰረቱ ሊሆን ይገባል፡፡ በሥራ ቦታ የሚሰጠውን ድጋፍና እንክብካቤ በተቋሙ ውስጥ የተቋቋሙ የተለያዩ ኮሚቴዎችና ቢሮዎች ሊደግፋት ይገባል፡፡ በመ/ቤቱ የሚካሄዱ የድጋፍና እንክብካቤ ሥራዎች ከሌሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በሚገኝ የፋይናንስ እገዛ ሊካሄዱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት በተቻለ መጠን የሠራተኛውን ቤተሰብ፣ የአካባቢውን ሕብረተሰብና በተለይም ወላጅ አልባ ሕጻናትን ሊያካትቱ ይገባል፡፡

## ክፍል ፫

## 7. የመመሪያው አጠቃላይ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

1) በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚካሄዱ ማናቸውም ፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞች ሁሉንም የሚኒስቴር መ/ቤቱን ሠራተኞችና ኃላፊዎች የሚያሳተፉ እና የፈጣን ተግባራዊ ምላሽ መርህን ከግንዛቤ እንዲያስገቡ ማድረግ፤
2) በሠራተኛው ስምምነት የኤድስ ፈንድ በማቋቋም፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለተጎዱ ሠራተኞች እና ወላጆቻቸዉን ላጡ ህፃናት የሠራተኛ ልጆች የሕክምና፣ የመድሃኒት፣ የተመጣጣኝ ምግብና ሌሎች ድጋፎች በዘላቂነት እንዲያገኙ ማድረግ፤
3) በመ/ቤቱ የሚካሄዱ ፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞችን ከጤና ፕሮግራም ጋር የተቀናጁ ማድረግ፣

4) ወረርሽኙን ከመከላከል አኳያ የሥራ ላይ መብቶች ጥበቃን ሊያጠናክር የሚችል ወቅታዊ የመመሪያ ማሻሻያ ማድረግ፣

5) በሴክተሩ የሚካሄዱ የፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞች የአካባቢውን ሕብረተሰብ ወረርሽኙን የመከላከል ጥረት የሚደግፍ እንዲሆን ማድረግ፣

6) የመ/ቤቱ አመራር አካላት ወረርሽኙን በመከላከል ረገድ ትኩረት እንዲሠጡና በቁርጠኝነት እንዲሳተፉ ማድረግ፣

7) ቀጣይነት ያለዉና የባህሪ ለዉጥ ሊያመጣ የሚችል የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራም ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ፣

8) በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት በማመቻቸት ሠራተኛዉ ራሱን በማወቅ ዘመናዊ የአኗኗር ባህል እንዲያዳብር ማድረግ፣

9) በሠራተኛው ስምምነት የሥራ ቦታ የኤድስ ፈንድ በማቋቋም የሕክምና፣ የመድሀኒት፣ የፋይናንስና ሌሎች ማኅበራዊ ድጋፎች በዘላቂነት እንዲኖር ማድረግ፣

10) የተጠናከረ ፀረ-ኤድስ የአጋርነት ግንኙነትና የቴክኒክ ትብብር ሥርዓት እንዲመሰረት በማድረግ ሁለንተናዊ የማስፈጸም አቅም ለመገንባት የሚያግዝ የእዉቀት፣ የሎጂስቲክስና የፋይናንስ ድጋፍ የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸትና በጀትን በቁጠባና በዉጤታማነት መጠቀም፣

11) ከስራ ባህሪያቸዉ አኳያ ይበልጥ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭ የሆኑና በሚያስከትለዉ ጉዳት ተጎጂ ለሆኑ ሠራተኞች ትኩረት በመስጠት በመከላከሉ እንቅስቃሴ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ፣

12) የፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞች አፈጻጸምን ለመመዘን የሚያስችል ወቅታዊ የግምገማ ስርዓት መዘርጋት፣

## ክፍል ፬

## ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሥራ ቦታዎች በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር፣ ሠራተኞችና ቫይረሱ በደማቸው የሚገኙ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

8. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር ሥልጣንና ተግባራት፣

1) መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከፍተኛ የሆነ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና፣ ፖለቲካዊ ቀውስ እንደሚያስከትል በመገንዘብ ቫይረሱን የመከላከሉን ስራ የመደበኛ ስራዉ አካል በማድረግ

በእቅድ ተይዞና በጀት ተመድቦለት በተቀናጀ መልኩ ተካትቶ (mainstreaming) ተግባራዊ እንዲደረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና አፈጻጸሞችን በየደረጃው መገምገም፤

2) ለፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መመሪያ ተግባራዊነት መከበር እና መሥሪያ ፈጣንና ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድና መቆጣጠር፤

3) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሥራ ቦታዎች ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ለችግሩ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞች እና የሥራ ቦታዎች ትኩረት እንዲሰጥ ማበረታታት፤

4) ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ሠራተኞች ከሌሎች ሠራተኞች ጋር እኩል መብትና ግዴታ ስላላቸዉ፦

   ሀ) በምልመላና በስራ ቅጥር ሥርዓት፤

   ለ) በሥራ ምደባ፤ በእድገት፤ ዝዉዉር፤

   ሐ) በደመወዝ ጭማሪና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች አሰጣጥ፤

   መ) በሥልጠናና በትምህርት ዕድል፤

   ሠ) ለሕዝባዊ አገልግሎት በሃላፊነት በመመረጥ፤

   ረ) የጤና አገልግሎት በመጠቀም፤

   ሰ) በሕግ፤ በአስተዳደር ደንብና ለሠራተኞች በተሠጡ ሌሎች መብቶች ላይ ምንም አይነት መድሎና ልዩነት እንዳይደረግ ማድረግ፤

5) ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችና ፕሮግራሞች የስርዓተ ፆታ እኩልነት መብትን የሚያራምዱና የሴት ሠራተኞችን ተሳትፎና ብቃት የሚያሳድጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

6) የማንኛዉም ሠራተኛ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ዉጤት ሁል ጊዜ በሚስጥር እንዲጠበቅ ማድረግ፤

7) መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚያደርጋቸዉ እንቅስቃሴዎች ሁሉም የሥራ ክፍሎች እንዲሳተፉ ማድረግ፤

8) ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ የሚገኝ ወይም የኤድስ ሕመምተኛ ሠራተኞች እና ቤተሰቦቻቸዉ አቅም በፈቀደ መጠን ማንኛዉንም ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ፤

9) በመ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፤

10) ሠራተኛዉ ኤችአይቪ/ኤድስን በዘላቂነት በባለቤትነት ስሜት ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲችል በተደራጀ መልኩ እንዲንቀሳቀስ የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠርለት ማድረግ፤

11) በመ/ቤቱ የሚካሄዱ ፀረ-ኤድስ ፕሮግራሞችንና ተግባራትን አፈጻጸም የሚያስተባብር፤ የሚከታተልና የሚቆጣጠር የሥራ ክፍል እና የፆታ ስብጥርን የጠበቀ፤ በፈቃዳቸው ለመሳተፍ የሚፈልጉና ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለ ሠራተኞችን ያካተተ፤ ከልዩ ልዩ

የሥራ ክፍሎች የተዉጣጣ ግብረ-ኃይል እንዲቋቋም ማድረግ፤ የቅርብ ግንኙነትም በመፍጠር ማጠናከርና ማበረታታት፣

12)አግባብ ካላቸዉ የሥራ ቦታ አጋሮች፣ ከመንግስት አስፈጻሚና ከፍትህ አካላት፣ ቫይረሱ በደማቸዉ ውስጥ በሚገኝ ወገኖች ከተመሰረቱ ማህበራትና ከሲቪል ማህበራት ጋር ቅንጅታዊ የትብብር ግንኙነት በመመስረት የጋራ ምክክር ሥርዓት መፍጠር፤

13)ወረርሽኙን በመከላከል፣ የሕክምና የድጋፍና እንክብካቤ እንዲሁም የሰብዓዊ መብት ጥበቃን የተመለከቱ ትምህርታዊ ዝግጅቶች እንዲካሄዱ መደገፍ፤

14)በመ/ቤቱ የሚካሄዱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራሞች በተቻለ አቅም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሠራተኞች ቤተሰቦችን ያካተቱ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤

15)በመ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራት በፆታ እኩልነት ላይ የተመሰረቱና አካል ጉዳተኞችን ከግንዛቤ ዉስጥ ያስገቡ መሆኑን ማረጋገጥ፤

## 9. <u>የመ/ቤቱ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የኤች.አይ.ቪ. መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን በማወቅ ለቫይረሱ ከሚያጋልጣቸው ሁኔታዎች እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን መጠበቅ፣

2) የቫይረሱን መስፋፋት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በተነደፉ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና መመሪያዎች ላይ በሚደረገዉ ውይይት ላይ በቅንነት በመመካከርና ከስምምነት ላይ በመድረስ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ግንባር ቀደም ተሳትፎ ማድረግ፤

3) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በመ/ቤቱና በሠራተኞች ላይ የሚያደርሰዉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጽዕኖ ለመዳሰስና ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን መስጠት፤

4) በመ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል ቫይረሱ በደማቸዉ ዉስጥ የሚገኝና ሕመምተኛ ለሆኑ ሠራተኞች እንዲሁም ወላጆቻቸዉን በኤድስ ሳቢያ ላጡ ልጆች ድጋፍና እንክብካቤ ለማድረግ አቅም በፈቀደ መጠን የሙያ፣ የፋይናንስና የማቴሪያል ድጋፍ ማድረግ፤

5) በመ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ ወቅታዊ መረጃዎች፣ የባህሪ ለዉጥን ሊያመጡ የሚችሉ ትምህርታዊ የሥልጠና ፕሮግራሞች፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የደም ምርመራ፣ የኮንዶም አቅርቦት፣ ድጋፍና እንክብካቤ እንዲሁም የሕክምና አገልግሎት እንዲኖር እና መሰረታዊ የስራ ላይ መብቶች እንዲተገበሩ አስተዋጽዖ ማድረግ፤

6) ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ዉስጥ የሚገኝና የኤድስ ሕሙማን የሆኑ ሰራተኞች እንዲሁም ሥራ ፈላጊዎችን ሰብአዊ መብት ማክበር፣ የአድልዎና የማግለል ተግባር አለመፈጸም፣ ተገቢ.ዉን ፍቅር፣ ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፤

7) በመ/ቤቱ ምቹ የስራ ሁኔታን በመፍጠር የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመቀነስ የሚደረገዉን ጥረት መደገፍ

8) ከሥራ ባህሪያቸው አንፃር ከደምና ከሰውነት የውስጥ ፈሳሽ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሠራተኞች የተፈቀደላቸውን የአደጋ መከላከያ መሳሪያ በአግባቡ መጠቀም፤

9) በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች፣ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች፣ ምክክሮችና ወቅታዊ መረጃዎችን በንቃት መከታተልና ተግባራዊ ማድረግ፣

10) መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚያዘጋጃቸው የአሰራር ማዕቀፎች ላይ በንቃት መሳተፍ፣

11) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚካሄደውን ጥረት ለማሳካት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሞያ፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣

12) በሥራ ቦታዎች በሴት ሠራተኞች፣ ተለማማጅ ሰልጣኝ ሠራተኞች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሥራ ፈላጊ አመልካቾችና ተገልጋዮች ላይ ወሲባዊ ጥቃትና ትንኮሳ ከመፈጸም መታቀብ፣

13) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የሥራ ቦታ መመሪያውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፡፡

## 10. ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

1) መ/ቤቱ በሚያዘጋጃቸዉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር እንቅስቃሴዎች ዉስጥ በንቃት መሳተፍ፤

2) ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ ልምድና ተሞክሮን በማጋራት በሥራ ቦታዎች የባህሪ ለዉጥ እንዲመጣ አርአያነት ያለዉ ተግባር ማከናወን፤

3) ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በየወቅቱ የምክር አገልግሎት ማግኘት እና የህክምና ክትትል ማድረግ፤

4) የበሽታዉን ስርጭት ከሚያባብሱ ድርጊቶች በመቆጠብና ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳይሠራጭ የበኩላቸዉን ጥረት ማድረግ፤

## ክፍል ፭

## በመ/ቤቱ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ግብረ-ኃይል አደረጃጀትና አሠራር

11. **ግብረ-ኃይል ስለማቋቋም**

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መ/ቤቶች የሥራ ቦታዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲችሉ ባወጣዉ መመሪያ ክፍል አራት፣ ተራ ቁጥር 4.1 መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭት መከላከያና መቆጣጠሪያ ግብረ-ኃይል ያቋቁማል።

12. **የግብረ-ኃይሉ አደረጃጀት**

1) የግብረ-ኃይሉ አባላት

የመ/ቤቱ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግብረ-ኃይል ተጠሪነቱ ለስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ሆኖ የሚከተሉትን አባላት ያካተተ ይሆናል።

ሀ/ የስርዓተ-ፆታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ኃላፊ - የግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ፤

ለ/ ከሁሉም የመ/ቤቱ የሥራ ክፍሎች የተወከሉ ሠራተኞች - አባላት፤

ሐ/ አንድ የተቀጠረ/የተመደበ ሠራተኛ (ፎካል ፐርሰን) አባልና ፀሐፊ ናቸዉ።

2) የግብረ-ኃይሉ ቢሮ

ግብረ-ኃይሉ ተግባርና ኃላፊነቱን በአግባቡና በተቀላጠፈ ሁኔታ መወጣት ያስችለዉ ዘንድ አንድ ቢሮ እና የእለት ተእለት ተግባራቱን የሚያከናውን መደበኛ ሠራተኛ ይኖረዋል።

3) የግብረ-ኃይሉ ተግባርና ሃላፊነት

ሀ/ግብረ-ኃይሉ የሚመራበትን የውስጥ ደንብ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የሥራ መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ በበላይ ኃላፊ ሲጸድቅም ተግባራዊ በማድረግ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ሐ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዳ የሥራ እቅድና አመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤ በእቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በማድረግ ለበላይ አመራሩ ሪፖርት ያቀርባል፣

መ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በዘርፉ ላይ የሚያሳድረውን ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ለመዳሰስና ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን በማሰባሰብ በመረጃ ላይ የተደገፉ ተግባራትን ለማከናወን የተለያዩ ጥናቶችን ያካሄዳል፣

ሠ/ የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት እንዲያስችል ተከታታይ ስልጠናዎች፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችና የውይይት መድረኮች ለሠራተኞች ያመቻቻል፣

ረ/ ሰራተኞች ራሳቸዉን ከኤች.አይ.ቪ. የሚከላከሉበትን እንዲሁም ቫይረሱ በደማቸዉ የሚገኝ ሠራኞች እና ህሙማን ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ሰ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አኳያ ልምድ ለመቅሰም ከሌሎች አግባብ ካላቸዉ አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤ ለሥራዉ አስፈላጊ የሆኑ የሙያ፣ የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፍና የፕሮጀክት እገዛ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በበላይ አመራሩ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሸ/ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ህሙማን የሆኑ ሠራተኞች ሰብዓዊ መብት መከበሩንና ተገቢው ድጋፍና እንክብካቤ የተደረገላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

ቀ/ የብሔራዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሥራ ቦታዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የሚመለከቱ ሌሎች የፌዴራል የህግ ድንጋጌዎችና የሚኒስቴሩ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያና የውስጥ ደንብ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

በ/ የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፈንድ ያቋቁማል፣

ተ/ ከመ/ቤቱ የበላይ አመራር የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ያከናውናል።

4) **የግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ ተግባርና ሀላፊነት**

የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግብረ-ኃይል ሰብሳቢ የግብረ-ኃይሉን ተግባርና ኃላፊነት በበላይነት ከመምራትና ከመቆጣጠር በተጨማሪ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ/ ቫይረሱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተነደፉ ፕሮግራሞችንና ዕቅዶችን በማጠናቀርና በማቀናጀት እንዲሠሩ ያደርጋል፤

ለ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሥራ ቦታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚካሄዱ ጥረቶችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሐ/ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሥልጠና መርሃ-ግብሮችን ይዘረጋል፣ የቅስቀሳና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ይሠራል፣ የማስተባበርና የማቀናጀት ተግባራትን ያከናውናል፤

መ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ የስራ ቦታ እቅዶችንና መርሃ-ግብሮችን አፈፃፀም በሚመለከት ተገቢዉን ክትትልና ግምገማ በማድረግ ለሚኒስቴሩ የበላይ አመራር ሪፖርት ያቀርባል፤

ሠ/ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጥር የወጡ እቅዶችን ማስፈፀሚያ የሚዉል ተጨማሪ የሃብት ምንጭ የሚገኝበትን መንገድ ያፈላልጋል፤

ረ/ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲበረታቱ ያደርጋል፤

ሰ/ በግብረሀይሉ የሚታወቁትን ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ የሚገኝና የኤድስ ህሙማን ሠራተኞች ማንኛዉም ጉዳይ በፈቃደኝነት ካልሆነ በስተቀር በሚስጥር እንዲያዝ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ሸ/ በተለየ ሁኔታ ለበሽታዉ ተጋላጭ የሆኑ አካላትን፣ ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ያገናዘበ ስልጠናና ትምህርት ይሰጣል/እንዲሰጥ ያደርጋል፤

5) የፎካል ፐርሰን ተግባርና ኃላፊነት

ሀ/ ተጠሪነቱ ለግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ/ለስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ሆኖ የግብረ-ኃይሉን መርሃግብር መሰረት በማድረግና ከሰብሳቢዉ ጋር በመመካከር የዕለት ተዕለት ሥራዎች ያከናውናል፣ የግብረ-ኃይሉን የስብሰባ ጊዜ ያመቻቻል፣ ስለአፈፃፀሙም ለግብረ-ኃይሉ ወርሃዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፤

ለ/ ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አጋር መ/ቤቶችና ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ቫይረሱን በመከላከል ረገድ ትምህርታዊና ሠራተኛዉን አሳታፊ የሚያደርጉ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፤

ሐ/ የግብረ-ኃይሉን ቃለ ጉባኤና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፣ አደራጅቶ በመረጃነት ይይዛል፤

መ/ የግብረ-ኃይሉን ሥራዎች በመደበኛነት ያቀናጃል፣ ያመቻቻል፤

ሠ/ የግብረ-ኃይሉን ዓመታዊ እቅድና በጀት በማዘጋጀት በግብረ-ኃይሉ አፀድቆ ለበላይ አካል/ለስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ያቀርባል፤

6) የግብረ-ኃይሉ ሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

ሂሳብ ሹሙ ከግብረ-ኃይሉ አባላት መካከል የሚመረጥና ተጠሪነቱ ለግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ሃላፊነቶች ይኖሩታል።

ሀ/ "በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፈንድ" በሚል ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤

ለ/ የሂሳብ ገቢና ወጪ በአግባቡ በመመዝገብ ይቆጣጠራል፤

ሐ/ በባንክ ሂሳብና ቼኮች ላይ ከግብረሀይሉ ሰብሳቢ ጋር በጣምራ ይፈርማል፤

መ/ ዓመታዊና የሶስት ወራት የሥራና የፋይናንስ ሪፖርት ለግብረሀይሉ አቅርቦ ያጸድቃል፤

ሠ/ አጠቃላይ የግብረሀይሉን የሂሳብ መዛግብት፣ ቼክን ጨምሮ ልዩ ልዩ ሰነዶችን በጥንቃቄ ይይዛል።

7) የግብረ-ኃይሉ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

ገንዘብ ያዥ ከግብረ-ኃይሉ አባላት መካከል የሚሰየም ሲሆን፣ ተጠሪነቱ ለግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች አሉት።

ሀ/ የግብረሀይሉን ገቢ ግብረ-ኃይሉ በሚያወጣቸዉ ህጋዊ ደረሰኞች ይሰበስባል፤

ለ/ ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰበዉን ገንዘብ በግብረሀይሉ የባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረግ ደረሰኞችን በጥንቃቄ ይይዛል፤

ሐ/ ለስራ ማስኬጃና ለግብረ-ኃይሉ ሥራ ጥቃቅን ወጪዎች የሚዉል ከብር 3000.00 (ሦስት ሺህ ብር) ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፤

መ/ የግብረ-ኃይሉን የየወሩን የወጪና ገቢ ሂሳብ ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን ያመሳክራል፤

ሠ/ በሂሳብ ሹሙና በግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ ጣምራ ፊርማ ሲታዘዝ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ/ እንዲከፈለዉ ለታዘዘለት ሰዉ ህጋዊ ደረሰኝ በመቀበል ወይም ለክፍያ በተዘጋጀ ሰነድ በማስፈረም ክፍያ ይፈጽማል፤

8) የሌሎች የግብረ-ኃይሉ አባላት ተግባርና ኃላፊነት

ከግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢና ጸሀፊ በተጨማሪ የሌሎች የግብረ-ኃይሉ አባላት ተግባርና ሃላፊነትን በተመለከተ እንደግብረሀይል አባልነታቸዉ አጠቃላይ የግብረሃይሉን መርህ፣ ዓላማና ዋና ዋና ተግባራት መሰረት በማድረግ በስብሰባዎች በመካፈል እና በዉይይት ዉሳኔዎችን በማሳለፍ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ሃላፊነታቸዉን መወጣት የሚጠበቅባቸዉ ሲሆን፣ በዋናነት ግብረ-ኃይሉ በሚመራበት የውስጥ ደንብ መሰረት እያንዳንዱ አባል የሚያከናውነዉ የሥራ ድርሻ ሊሰጠዉ ይችላል።

9) የግብረ-ኃይሉ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

ሀ/ ግብረ-ኃይሉ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ የሚኖረዉ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። በዓመት አንድ ጊዜ ከሠራተኞች ጋር አጠቃላይ ስብሰባ ይኖረዋል።

ለ/ የግብረ-ኃይሉ ስብሰባ በሰብሳቢዉ ወይም ሰብሳቢዉ በማይኖርበት ጊዜ እሱ በጽሁፍ በሚወክለዉ አባል ይመራል።

ሐ/ ግብረ-ኃይሉ የሚያካሂደዉ የመደበኛ ስብሰባ ጥሪና አጀንዳ በግብረ-ኃይሉ ፀሀፊ አማካኝነት ቢያንስ ከስብሰባዉ እለት ሁለት ቀን በፊት ለተሰብሳቢዎች ሊሰጣቸዉ ይገባል።

መ/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ለግብረ-ኃይሉ አስረድቶ ተቀባይነት ካላገኘ በስተቀር ማንኛዉም አባል የመደበኛም ሆነ የአስቸኳይ ስብሰባ ጥሪ ደርሶት መቅረት አይችልም።

ሠ/ ያለ በቂ ምክንያት በተደጋጋሚ በስብሰባ የማይሳተፍ አባል ሲኖር ከአባልነት እንዲነሳ ይደረጋል።

ረ/ በማንኛዉም የግብረ-ኃይሉ ስብሰባዎች ከአባላቱ ከግማሽ በላይ (50+1) ከተገኙ ስብሰባዉ ይቀጥላል።

ሰ/ ማናቸዉም የግብረ-ኃይሉ የስብሰባ አጀንዳዎች ዉይይት ተደርጎባቸዉ ዉሳኔ የሚያገኙት ከዕለቱ ተሰብሳቢዎች በሶስት አራተኛ ድምጽ የተደገፉ ሲሆን ብቻ ነዉ።

ሸ/ ማንኛዉም የግብረ-ኃይሉ ስብሰባዎች በግልጽነትና በተጠያቂነት እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ዉይይት የሚካሄድባቸዉ ሲሆን፣ በፀሀፊው አማካኝነት ቃለ ጉባኤ ተይዞ ስብሰባዉ በተጠናቀቀ በሁለት ቀናት ዉስጥ ተሰብሳቢዎች ፊርመዉበት በሰነድነት መቀመጥ ይኖርበታል።

10) የግብረ-ኃይሉ የሥራ ክፍልና ልዩ ልዩ መገልገያዎች

ሀ/ ግብረ-ኃይሉ መደበኛ ተግባሩን የሚያከናዉንበት ቢሮ ይኖረዋል።

ለ/ የግብረ-ኃይሉ አባላት ሙሉ ጊዜአቸዉን ቢሮአቸዉ ዉስጥ ሆነዉ መደበኛ ሥራቸዉን ሲያከናዉኑ፣ ለተገልጋዮች ተገቢዉን አገልግሎት የሚሰጥ ፎካል ፐርሰን የተዘጋጀውን ቢሮ በመንግስት መደበኛ የሥራ ሰዓት ክፍት አድርጎ አገልግሎት ፈላጊዎችን ያስተናግዳል።

ሐ/ ግብረ-ኃይሉ ለቢሮዉ ስራ ማከናወኛ ከመ/ቤቱ የሚሰጡትን ንብረቶች በሃላፊነት ተረክቦ በጥንቃቄ አገልግሎት ላይ ያዉላል።

መ/ ለስራዉ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተጨማሪ የመገልገያ ቁሳቁሶችን፣ ግብረ-ኃይሉ ከበጎ አድራጊ ተቋማት በእርዳታ የሚያገኝበትን መንገድ በማፈላለግ እንዲሟሉ ያደርጋል።

ሠ/ በእቅድ የያዛቸዉን ተግባራት ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑና ከሌሎች በድጋፍ /በስጦታ/ ማግኘት ያልቻለውን፣ የበጀት አቅሙ ለመግዛት የማያስችለውን ፤የመገልገያ መሳሪያዎች ግገር ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀርባል።

11) የውሎ አበል

የግብረ-ኃይሉ አባላት ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ስራ ጋር በተያያዘ ከአዲስ አበባ ከተማ ዉጪ ወደተለያዩ ስፍራዎች ሲንቀሳቀሱ የዉሎ አበል ይከፈላቸዋል።

12) የግብረ-ኃይሉ የበጀት ምንጭ

የግብረ-ኃይሉ የበጀት ምንጭ፦

ሀ/ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመደብ መደበኛ በጀትና በስጦታ መልክ ከሚገኝ የማቴሪያልና ገንዘብ ድጋፍ፤

ለ/ ከሠራተኞች በፈቃደኝነት በየወሩ ከሚሰበሰብ መዋጮ፤

ሐ/ በበጎ አድራጊ ድርጅቶች ከሚደረግ የፋይናንስ፣ የማቴሪያል እና የገንዘብ እገዛ ...ወዘተ. ይሆናል።

13) የግብረ-ኃይሉ የፋይናንስ አሰራር

ሀ/ ግብረ-ኃይሉ በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 13 ንዑስ ቁጥር 6/ሀ መሰረት የራሱን የባንክ አካዉንት ይከፍታል።

ለ/ የባንክ ሂሳቡ በግብረ-ኃይሉ ሰብሳቢ/በስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ኃላፊና በሂሳብ ሹሙ ፊርማ ብቻ የሚንቀሳቀስ ይሆናል።

ሐ/ የገንዘብ ሂሳብ አሰራሩ በመደበኛዉ የጥንድ ሂሳብ (Double entry) የሚሰራ ይሆናል፡

14) የግብረ ሀይሉን ሂሳብ ኦዲት ስለማድረግ

ሀ/ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኦዲት መምሪያ በሚኒስትሩ ትእዛዝ፣ ወይም በግብረሀይሉ ጥያቄ ወይም በራሱ ተነሳሽነት የግብረ-ሀይሉን አጠቃላይ ሂሳብ ይመረምራል፣ ዉጤቱን ለሚኒስትሩ ያቀርባል።

ለ/ በዉጤቱም መሰረት ተገቢዉ እርምጃ ይወሰዳል።

## ክፍል ፮

## 13. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ

በኤች.አይ.ቪ. ምክንያት ታማሚ ለሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ወላጅ አልባ ለሆኑ ሌሎች ህፃናት አቅም በፈቀደ መጠን ቁሳዊና ሞራላዊ እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ ቫይረሱን ከመዋጋት አንጻር ከፍተኛ አወንታዊ ጎን ያለዉ በመሆኑ ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ ይገባል። ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረገዉም የሚከተሉትን ነጥቦች እና በተራ ቁጥር 17 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ይሆናል።

1) ድጋፍና እንክብካቤ የሚጠይቁ ሠራተኞች (ቤተሰቦቻቸው) የድጋፍ ጥያቄአቸውን ሊያቀርቡ የሚችሉበት ግልጽ አሰራር መዘርጋት፣ በየጊዜዉም እየፈተሹ ማሻሻል፣

2) ድጋፍና እንክብካቤ የሚጠይቁ ሠራተኞችን (ቤተሰቦቻቸውን) የችግር ዓይነትና መጠን በማስረጃ በተደገፈ መልኩ ማጣራትና መለየት፣

3) ለድጋፍና እንክብካቤ የተለዩ ሠራተኞችን /ቤተሰቦቻቸዉ/ እንደችግራቸዉ አጣዳፊነትና ክብደት ከአድሎ በጸዳ መልኩ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣

4) የድጋፍና እንክብካቤ ዓላማው ይሳካ ዘንድ ድጋፉን በቀጥታ ለተረጂዉ /ለተጎጂዉ/ ሰዉ ወይም ሰዎች እንዲደርስ ማድረግ ወይም መስጠት፣

5) በተደረገዉ እንክብካቤና ድጋፍ ተረጂዉ ወገን ምን ያህል በአግባቡ እንደተጠቀመበት እና ከዚህም ጋር በተያያዘ ድጋፍና እንክብካቤዉ እያመጣ ያለዉን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ዉጤት መገምገምና ተገቢዉን መረጃ መያዝ፣

6) ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸዉ ወገኖች የተረጂነት ስሜት አድሮባቸው የሰዉ እጅ ጠባቂ እንዳይሆኑ፣ እንደአስፈላጊነቱ ደረጃ በደረጃ ከተረጂነት ተላቀዉ የራሳቸዉ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸዉ ከሌሎች አጋሮች ጋር በመሆን ተገቢዉን ጥረት ማድረግ፣

7. ለድጋፍና እንክብካቤ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሚሰበሰበው የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ለታቀደለት ዓላማ ብቻ በአግባቡ ይዉሉ ዘንድ በግልጽነትና በተጠያቂነት መርህ ላይ በመመስረት በቁጠባ መጠቀም፣

8) እንደ አስፈላጊነቱ የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጡን ሊያግዙ የሚችሉ ሌሎች አዎንታዊና ጤናማ አካሄዶችን መከተልና ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

## 14. ለድጋፍና እንክብካቤ ብቁ ስለመሆን

የኤድስ ህመምተኛ የሆነ የመ/ቤቱ ሠራተኛ ወይም ሠራተኛው ከሞተ በኋላ ቤተሰቦቹ ሊረዱ የሚችሉት የገቢ መጠናቸዉና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸዉ በአግባቡ ተጠንቶና የችግራቸዉ መጠንና አንገብጋቢነት ታይቶ እንደየቅደም ተከተላቸዉ ቅድሚያ በመስጠት ይሆናል። በመሆኑም ድጋፍ የሚሰጠዉ:-

1) **የኤድስ ሕመምተኛ ለሆኑ ሠራተኞች፤** ቫይረሱ በደሙ ዉስጥ የሚገኝ ሠራተኛ በተለያዩ የጤና ችግሮች የተነሳ የኤድስ ህመምተኛ መሆኑ በምርመራ ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

2) **በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሳቢያ የመ/ቤቱ ሰራተኛ በሞት ሲለይ/ስትለይ ለቤተሰብ፤** ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ወይም ቤተሰቦች ሌላ ለመኖር የሚያስችላቸዉ የገቢ ምንጭ የሌላቸዉ በመሆኑ ምክንያት ለዕለታዊ የኑሮ ችግር የተጋለጡ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

3) በቁጥር ለተወሰኑ ወላጅ አልባ ህፃናት፣

## 15. የድጋፍና እንክብካቤ ጥያቄ አቀራረብ

በቫይረሱ ምክንያት ህመምተኛ የሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸዉ ድጋፍ ሊያገኙ የሚችሉት ጥያቄያቸዉን በፅሁፍ አድርገዉ ከተገቢዉ ማስረጃ ጋር ለጸረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግብረኃይል ሰብሳቢ/ለስርዓተ ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ኃላፊ ሲያቀርቡ ብቻ ይሆናል፡፡ ለዚህም፡-

1) ድጋፍና እንክብካቤ ጠያቂዉ ሠራተኛ ሊደረግለት የሚፈለገዉን የድጋፍና እንክብካቤ አይነት የሚገለጽ የጽሁፍ ማመልከቻ በግንባር ወይም በሚወክለዉ ሰው አማካኝነት ለግብረ-ሀይሉ ሰብሳቢ/ለስርዓት ጾታ ሜይንስትሪሚንግ መምሪያ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፣
2) ከድጋፍ ጥያቄዉ ማመልከቻ ጋር አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ዋና እና ፎቶ ኮፒ ተያይዘዉ መቅረብ አለባቸዉ፡፡ የማስረጃዎቹ ትክክለኛነት ከተረጋገጠ በኋላ ዋናዎቹ ለባለጉዳዩ የሚመለሱ ይሆናል፡፡
3) በቃል የሚቀርቡ የድጋፍና እንክብካቤ ጥያቄዎች ተቀባይነት የላቸዉም፡፡

## 16. የድጋፍ አሰጣጥ መስፈርቶች

1) የድጋፍ ጠያቂዉ የገቢ መጠን፣
2) ያለበት የጤንነት ሁኔታና የሃኪም አስተያየት፣
3) የቤተሰብ ሁኔታና ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ብዛት፣
4) ከሌሎች ድጋፍ አድራጊ ተቋማት የሚያገኘዉ ድጋፍ ካለ አይነትና መጠን፣
5) ከተረጂዉ አንጻር መሠረታዊና አስፈላጊ ተብለዉ ሊወሰዱ የሚችሉ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

## 17. የድጋፍና እንክብካቤ አይነቶች

ከላይ በተራ ቁጥር 15 እና 17 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ በቫይረሱ ምክንያት ህመምተኛ የሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞች፣

1) ለጤናቸዉ ተስማሚ በሆነ የሥራ አካባቢ እንዲሰሩ ማድረግ፣
2) የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸትና ተጠቃሚ ማድረግ፣
3) የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣
4) እንደአስፈላጊነቱ የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣

## 18. በገንዘብ የሚደረግ ድጋፍ

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ድጋፍ ፈንድ በጊዜም ሆነ በመጠን የሚያደርገዉ የገንዘብ ወይም የአይነት ድጋፍ ከሰራተኛው መዋጮ

እና ከሌሎች በሚያገኘዉ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍና ዕርዳታ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ድጋፉ እንደገቢዉ ሁኔታ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡ በመሆኑም፡-

1) በቫይረሱ ምክንያት ህመምተኛ የሆነና ቤተሰብ የመሰረተ ሠራተኛ ድጋፍ በጠየቀ ጊዜ በወር የ300.00 ብር (ሦስት መቶ ብር) ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ አቅም በፈቀደ መጠን ተጨማሪ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2) ድጋፍ ጠያቂዉ ሠራተኛ በሕይወት እያለ ቤተሰብ ያልመሰረተና የሚያስተዳድራቸዉ አረጋዉያን ካሉ በወር ብር 200.00፣
3) ቤተሰብ መስርቶ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ለተለየ ሠራተኛ:-

ሀ/ ከ1-4 ለሚሆኑ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ለእያንዳንዳቸዉ በወር ብር 100.00፣

ለ/ ከ4 በላይ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በድምሩ በወር ብር 500.00፣

ሐ/ የሚች ሕጋዊ የትዳር ጓደኛ ምንም የገቢ ምንጭ የሌለዉ/የሌላት ከሆነ/ከሆነች በወር ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

4) ወላጅ አልባ የሆኑ ሌሎች ህፃናት ግብረ-ኃይሉ በሚወስነው መሠረት የሚረዱ ይሆናል፡፡
5) ግብረ-ኃይሉ የገቢ መጠኑን መሠረት በማድረግ ለተረጂዎች ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግበትን ሁኔታ በየወቅቱ እየተወያየ በመወሰን ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡፡
6) ግብረ-ኃይሉ በዓይነት ድጋፍ ሊያደርግ የሚችልበት ሁኔታና አቅም ካገኘ ከገንዘብ ድጋፍ ጋር በተመጣጠነ መልኩ የዓይነት ድጋፍ ማድረግን በተመለከተ፣ እንደሁኔታዉ ተወያይቶ የሚወስነዉ ይሆናል፡፡

## 19. ድጋፍና እንክብካቤ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

1) ድጋፍ የሚደረግለት ሠራተኛ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይና ቤተሰብ የሌለዉ ከሆነ፣
2) ድጋፍ የሚደረግለት ሠራተኛ የተሻለ የገቢ ምንጭ ወይም ድጋፍ በቋሚነት የሚያገኝበት ሁኔታ ሲፈጠርና ይህም በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፣
3) ይረዱ የነበሩ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ዕድሜያቸው 18 ዓመት መድረሱ ሲረጋገጥ፣
4) ይረዱ የነበሩ አረጋዉያን ወላጆች፣ ባል/ሚስት በሞት ከተለዩ፣
5) ድጋፍ የሚደረግለት ሠራተኛ ወይም ቤተሰቡ፣ የሚደረግለትን የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ለታቀደለት ዓላማ ከማዋል ይልቅ ከዓላማዉ ተጻራሪ ለሆነ እና ችግሩን ሊያባብስ በሚችል ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚያዉል መሆኑ በማስረጃ በተደገፈ ሁኔታ ሲቀርብና በግብረሀይሉ ሲታመንበት ይሆናል፡፡

## ክፍል ፮

## የዲሲፕሊንና ቅሬታ ሥርዓቶች

### 20. የዲሲፕሊን ጥፋት

1) የሥራ ቦታዎችን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለመከላከልና አድሎአዊ አሠራሮችን ለማስቀረት እንዲቻል በመ/ቤቱ ሥራ ቦታ ላይ ኤች.አይ.ቪን ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ድርጊቶች እንዲሁም ማንኛቸዉም አድሎአዊ አሠራሮች ሰብአዊ መብትን የሚጥሱ ተግባራት በመሆናቸዉ የሥራ ቦታ ጥፋቶች ናቸዉ፤
2) ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ተያይዘዉ የሚፈጸሙ ጥፋቶች በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 68 ላይ ከተደነገጉት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ጋር እኩል ክብደት ያላቸዉ ጥፋቶች ናቸዉ፤
3) በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የመንግስት መ/ቤቶች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ላይ በተቀመጠዉ መሰረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ቦታዎች በማናቸዉም ሁኔታ ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ኤች.አይ.ቪን ለማስተላለፍ የሚደረጉ ድርጊቶችን መፈጸም በከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስቀጣ ተግባር ነዉ፡፡
4) በመደበኛ ስራዎች ላይ እንዲሁም ቅጥር፣ እድገትና ዝዉዉር በማስታከክ በሴቶች ላይ ፆታዊ ጥቃት መፈጸም ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ነዉ፡፡
5) በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ለሚገኝ እና ለኤድስ ሕሙማን ሰራተኞች የተረጋገጡላቸዉን መብቶች ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት መጣስ በከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስቀጣ ተግባር ነዉ፡፡

### 21. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቶች

1) ከኤችአይቪ/ኤድስ ጋር የተያያዙ ጥፋቶች ወይም አድሎአዊ አሠራሮች የተፈጸመባቸዉ ሠራተኞች አቤቱታቸዉን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የማቅረብና የተሰጠዉን ምላሽ በጽሁፍ የማወቅ መብት አላቸዉ፡፡
2) የመ/ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴም ድርጊቱ መፈጸሙን ካመነ በአጥፊዉ ሠራተኛ ወይንም ኃላፊ ላይ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 68/14 መሠረት የዲሲፕሊን ክስ እንዲቀርብ ጉዳዩን ለመ/ቤቱ የአስተዳደር አካል ወይም ሕግ አገልግሎት ይመራል፣ በዲስፕሊን ተጣርቶ ሲቀርብለትም ዉሣኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ፰

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 22. መመሪያዉ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ይህ መመሪያ ሻይረሱ በህክምና ረገድ በሚኖረዉ ለዉጥ እንዲሁም በየጊዜዉ የሚወጡ ሕጎችን እና ሌሎች ገዥ/ወሳኝ ጉዳዮችን ግምት ዉስጥ በማስገባት እንደ አስፈላጊነቱ የሚሻሻል ይሆናል።

### 23. መመሪያዉን ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይህንን መመሪያ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸዉ።

### 24. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሰኔ 27 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር